# የአመክሮ ሕጎችና አተገባበራቸው በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት

*በላይነህ አድማሱ እጅጉ*♣*
*ዓለሙ ዳኛው ፈለቀ*♣*

**አህጽሮተ-ፅሁፍ**

*በኢትዮጵያ አመክሮ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው መልካም የሚባል የባሕርይ መሻሻል በማሳየታቸው 2/3ኛውን የእሥራት ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ቀሪውን የፍርዱን 1/3ኛ ወይም በፍርድ ቤት የሚወሰነውን የሙከራ ጊዜ በአመክሮ ከእስር ተለቅቀው በሙከራ እንዲያሳልፉ የሚደረግበት አሰራር ነው፡፡[1] ጥናቱ በተደረገበት በአማራ ብሄራዊ ክልል አንዱ በሆነው የባሕር ዳር ማረሚያ ቤትም ይኸው ተግባራዊ ይደረጋል። ይሁን እንጂ በአመክሮ አተገባበርና ሕጉ ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም በክልሉ አመክሮ አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ የሕግ ክፍተቶችንና በማረሚያ ቤቱ አሉ የሚባሉ የአፈጻጸም ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሐሳቦችን ለመጠቆም ነው። በማረሚያ ቤቱ የአመክሮ ሕጎችና አፈጻጸማቸው ምን እንደሚመስል በአይነታዊ የጥናት ዘዴ ለመመርምር ተሞክሯል። የጥናቱ መረጃዎችም በሳይንሳዊ መንገድ ተተንትነዋል። በዚህም መሰረት በወንጀል ሕጉና በአብክመ አመክሮ አሰጣጥ መመሪያ መካከል አለመጣጣምና የሕግና የአፈጻጸም ክፍተቶች መኖራቸውን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡*

***ቁልፍ ቃላት፡-*** *አመክሮ፣ ማረሚያ ቤት፣ የእስራት ቅጣት፣ ታራሚ፣ መልካም ጸባይ*

## መግቢያ

የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ወንጀልን የመከላከልና ወንጀለኞችን በፍርድ ሂደት ለይቶ እንዲታረሙና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ የማድረግ ዓላማን ለማሳካት የሚደራጅ ሥርዓት ነው፡፡[2] እነዚህን ዓበይት ዓላማዎች ለማሳካት በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ጉልህ ሚናና ኃላፊነት ያላቸው አካላት ማለትም ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤትና ማረሚያ ቤቶች ይዋቀራሉ፡፡[3]

እነዚህ የፍትህ አካላት ለአንድ ዓላማ የተቋቋሙ ሲሆን የተለያዩ ነገርግን ተያያዥነት ያላቸው ተልእኮዎች ወይም ተግባራት ታላሚ አድርገው ይሰራሉ፡፡ ሁሉም የፍትህ አካላት ወንጀልን በመከላከልና ወንጀል ፈጻሚዎችን በፍትህ ሥርዓቱ እንዲታረሙ በማድረግ የሕግ

---

♣ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (አዲስ አበባ ዩኒብረሲቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ሕግ (አምስተርዳም ዩኒቨርሲቲ)፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ badmaasu7@gmail.com ወይም belaynehv@yahoo.com

♣ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (ጅማ ዩኒቨርሲቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር እና ሰብአዊ መብት ሕግ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ)፣ ሌክቸረር፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ alemudag@gmail.com

[1] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1997፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣1997 ፣ አንቀፅ 202 እና 204 (ከዚህ በኋላ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ)

[2] Alfred Blumstein, 'Systems analysis and criminal justice system', *the annals of the American Academy of political and social science*, Vol. 374 (1997), pp. 93-94, available at http://www.jstor.org/stable/1037196 last accessed on 17-06-2017)

[3] Thomas J. Bernard and Robin Shepard, 'Conceptualizing criminal justice theory', *Justice Quarterly,* Vol. 18 No 1, (March 2001), p.2 , http://www.UC.edu/content/dam/uc/.../articles/. Last accessed on 17 June 2017)

የበላይነትን ለማረጋገጥና ፍትህን ለማስፈን የተቋቋሙ ናቸው፡፡[4] ለዚህ ዓላማ እውን መሆን ፖሊስ ወንጀልን የመከላለከልና ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ተጠርጣሪዎችን በመያዝ ሳይንሳዊ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በማስረጃ የተደገፉ እውነታዎችን ፈልጎ[5] የምርመራ ውጤቱን ለዐቃቤ ሕግ ያቀርባል፡፡[6] የወንጀል የምርመራ መዝገብ የሚደርሰው ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ ወንጀል መፈጸሙን፣ እንዴትና በማን እንደተፈጸመ የሚያሳይ ማስረጃ እንዳለ ባመነ ጊዜ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ[7] ተከራክሮ አጥፊው ጥፋተኛ እንዲባል[8] እና ሊያርመው የሚችል ቅጣት እንዲወሰንበት በማድረግ የማረም ሂደቱም በአግባቡ እንዲከናወን አስፈላጊውን ክትትል የማደረግ ኃላፊነት አለበት፡፡[9] ፍርድ ቤቶችም በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የግራቀኙን ማስረጃ በመቀበልና በአግባቡ በመመዘን ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ተመጣጣኝ የሆነውንና የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማ ሊያሳካ የሚችል ቅጣት በጥፋተኛው ላይ ይወስናሉ፤[10] ማረሚያ ቤቶችም በፍርድ ቤቱ የተወሰነውን ቅጣት በሕጉ መሠረት በማስፈጸም ጥፋተኛው መልካም ዜጋ እንዲሆን የማረም ሥራቸውን በሀላፊነት ይፈጽማሉ፡፡[11] በአጠቃላይ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አካላቱ ከላይ የተመለከቱትን አበይት ተግባራት እጅና ጓንት ሆነው በመሥራት የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

አሁን ባለው የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓትም ከላይ የተመለከቱትን ተግባራት የሚያከናውኑ የፍትህ አካላት በፌደራልና በክልል ደረጃ ተዋቅረው የእለት ተእለት ተግባራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሠረት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት እነዚህ የፍትህ አካላት በየአስተዳደር እርከኑ ተዋቅረው በሕግ የተሰጣቸውን መሰል ተግባራት በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ ተግባራቱ ሲከናወኑ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች እንደሚከሰቱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡[12] በተጨማሪም በማረሚያ ቤቱ በኩል በሚከናወኑ ተግባራት በተለይም በአመክሮ አሰጣጥ ሥርዓት ላይ ታራሚዎች ቅሬታ እንደሚያሰሙ በመስክ ምልከታ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በታራሚዎች በኩል ከሚነሱ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ በወንጀል ሕጉና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የአመክሮ አሰጣጥ

---

[4] Nicola Lacey, Criminal Justice and Democratic Systems: Inclusionary and Exclusionary Dynamics in the Institutional Structure of Late Modern Societies, Center for European Studies Working Paper Series #148 (2007)

[5] Melissa-A.-settle,M.Ed, Police-officers-Then and now, Teacher Created Materials, publishing Inc., 2007, pp 6-11

[6] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 185/1954፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣1954፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አንቀጽ 37(2)

[7] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 40፣ 109-120፣ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 943/2007፣ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣2007፣ አንቀጽ 6 (ከዚህ በኋላ 'የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መቋቋሚያ አዋጅ')

[8] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ የሚኒስትሮች ምክርቤት፣ የካቲት 25/2003 ዓ.ም፣ ቁጥር 3.10 ( ከዚህ በኋላ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ)፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መቋቋሚያ አዋጅ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7 እንደተገለጸው

[9] የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ዝኒከማሁ፣ ቁጥር 5.3 (መ)፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መቋቋሚያ አዋጅ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7 እንደተገለጸው

[10] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 6 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 149

[11] የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 365/1995፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1995፣ አንቀጽ 6፣ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ እንደተገለጸው፣ ቁጥር 5.3

[12] Federal Democratic Republic of Ethiopia, comprehensive justice system reform program baseline study report, Ministry of Capacity Building Justice system reform program office February, 2005, pp. 14-17

ሥርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣ ጊዜያዊ መመሪያ (ከዚህ በኋላ የአብክመ የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ እየተባለ የሚጠራ) ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን፣ የአመክሮ ጊዜ ስሌትና የማስረጃ አቀራረብ፣ እንዲሁም ከማረሚያ ቤት ከወጡ በኋላ ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖራቸውን መስተጋብርና ሌሎችንም የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ችግሮቹን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሐሳብ በማፈላለግ ለሕግና ለፖሊሲ አውጭዎች እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት መጠቆሙ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት አመክሮን የሚመለከት ምርምር በማድረግ የተገኘው ውጤት በጽሑፉ ቀርቧል፡፡

በጥናቱ የተዳሰሱ መሠረታዊ ነጥቦችም፤ የአመክሮ ቅድመሁኔታዎች ግልጽ መሆን አለመሆን፣ ቅድመ ሁኔታዎቹ ለአፈጻጸም ቀላልና ምቹ መሆን አለመሆናቸው፣ ለአመክሮ ተጠቃሚነት ብቁ የሚሆኑ ታራሚዎች የሚለዩበት ማንነት፣ ታራሚዎች ለወንጀል ሰለባዎች ካሳ ለመክፈል ያላቸው ግዴታ በአመክሮ አሰጣጥ ላይ የሚኖረው ሚናና ተፈጻሚነት፤ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ነጥቦች ለመቃኘት በየደረጃው ከሚገኙ የማረሚያ ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የአመክሮ ተጠቃሚ ለመሆን በዝግጅት ላይ ያሉትን ታራሚዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሌሎች አካላት በማነጋገር መረጃ መሰብሰብ የጥናቱ ዋና ተግባር በመሆኑ አይነታዊ የመረጃ አሰባሰብ ስልት ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መሠረት በጥናቱ አግባብነት ያላቸውን ልዩ ልዩ የጽሑፍ ሰነዶች በመፈተሽ፤ቃለመጠይቅ፣ የቡድን ውይይት (Focus group discussion) እና ምልከታ በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

## 1. የአመክሮ ትርጉምና ጽንሰ-ሐሳብ

በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው በማረሚያ ቤት አስተዳደር ከሚከናወኑ በርካታ ተግባራት መካከል አመክሮ አንዱ ነው፡፡ ማረሚያ ቤት ታራሚዎችን ከመጠበቅ ባሻገር ለጠቅላላ ሰብዕናቸው ግንባታ የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት፣ ልዩልዩ የሙያ ሥልጠናና ሌሎችንም የገቢ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ ሥራዎችን እንዲሰሩና ራሳቸውን እንዲያግዙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡[13] ይህንን አቢይ ኃላፊነት ለመወጣት በሚያከናውናቸው ተግባራት የታራሚዎችን ባሕርይ በማሻሻል መልካም ዜጋ ማድረግ የሚጠበቅ ውጤት[14] ሲሆን፣ ይህንን የባሕርይ ለውጥ ማሳየት የቻሉ ታራሚዎችን ሙሉ የእሥራት ጊዜያቸውን መፈጸም ሳይጠበቅባቸው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ ለማድረግ አመክሮን የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡[15] በዚህ መሠረት የብዙ ሀገር ማረሚያ ቤቶች በአይነትና በይዘቱ የተለያየ ይሁን እንጂ ታራሚዎችን እያነጹ መልካም ዜጋ በማድረግ ለታራሚዎቹና ለማህበረሰቡ ጥቅም ሲባል የእሥራት ጊዜያቸው ከማለቁ በፊት አመክሮን ይሰጣሉ፡፡[16] በኢትዮጵያ ባሉ

[13] የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 6፣ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 8 ላይ እንደተገለጸው፣ ቁጥር 5.3 እና የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 እንደተገለጸው፣ መግቢያውና አንቀጽ 1

[14] የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 8 ላይ እንደተገለጸው፣ ቁጥር 5.3

[15] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 202፣ የኢፌዴሪ ሚኒስትሮች ም/ቤት፣ የፌዴራል ታራሚዎችን አያያዝ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 138/1997፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አንቀጽ 46 (ከዚህ በኋላ የፌዴራል ታራሚዎችን አያያዝ ለመወሰን የወጣ ደንብ እየተባለ የሚጠራ) እና በአብክመ አስተዳደርና ጸጥታ ቢሮ የአመክሮ አሰጣጥ ሥርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣ ጊዚያዊ መመሪያ ቁጥር 1/2003 ዓ.ም (ከዚህ በኋላ የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ) መግቢያ

[16] Correctional Services of Canada, National Parole Board. 2007 from confinement to community. Available at http://www.npb-cnlc.gc.ca /infocntr/confinement_community_e.htm last accessed on 2 July 2007.

ቁጥራቸው 119[17] በሚደርሱ ማረሚያ ቤቶችም በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግንና አመክሮን ለማሳለጥ በወጡ ልዩ ልዩ የሥራ መመሪያዎች አማካይነት አመክሮ ይሰጣል፡፡

ለመሆኑ አመክሮ ምንድን ነው? ስለአመክሮ የሕግ ጽንሰ ሐሳብና አፈጻጸሙ ከማውሳት አስቀድሞ ጥያቄውን ለመመለስ ሥለጠቅላላ ትርጉሙና በጥቂቱ ማውሳቱ የጥናቱን ዓላማ ለመረዳት የሚኖረው ፋይዳ ቀላል አይሆንም፡፡ በመሆኑም አመክሮን የዘርፉ ባለሙያዎች እንዴት እንደሚረዱትና እንደሚገልጹት እንደሚከተለው ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

አመክሮ አንድ ታራሚ የእሥራት ጊዜውን ሙሉ በሙሉ ከመፈጸሙ በፊት በገደብ ወይም በሁኔታ ላይ ተመስርቶ ከእስር የሚለቀቅበትና ገደቡን ተላልፎ ሲገኝ እንደ አስፈላጊነቱ ወደነበረበት ማረሚያ ቤት እንዲመለስ የሚደረግበት አሠራር ነው፡፡[18] በፕሪቶሪያ አመክሮ ቦርድ ማኑዋል ላይም ለቃሉ የሚከተለው ትርጉም ተሰጥቶታል፤

> አመክሮ አንድ ታራሚ በፍርድ ቤት ከተጣለበት የእሥራት ቅጣት በሕግ እንዲፈጽም የሚገደደውን ዝቅተኛ የእሥራት ጊዜ ከፈጸመ በኋላ ያሳየው የባሕርይ መሻሻል ታይቶ ቀሪውን የእሥራት ጊዜ ከማረሚያ ቤት ውጭ በመሆን ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲፈጽም በሁኔታ ወይም ያለሁኔታ ከእስር ተለቅቆ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ተቆጣጣሪ ክትትል እንዲቆይ የሚደረግበት የቅጣት አፈጻጸም ሥርዓት ነው፡፡[19]

ኒል ልዊስ ማንዴልኮ የተባለ ተመራማሪም እንዲሁ ለአመክሮ ከዚህ በላይ ከተመለከተው ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ አለው፡፡[20]

ከላይ ከቀረቡ ትርጉሞች መረዳት እንደሚቻለው፣ አመክሮ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች መያዝ ወይም ማሟላት እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለአመክሮ ጽንሰ ሐሳብ ማእዘን ሆኖ የሚያገለግለው በፍርድ ቤት በታራሚው ላይ የሚወሰነው የእሥራት ቅጣት ነው፡፡ አንድን ወንጀል የፈጸመ ሰው በፈጸመው ወንጀል ተከስሶ በፍርድ ቤት የእሥራት ቅጣት ተወስኖበት ወደ ማረሚያ ቤት እንዲላክ ካልተደረገ የአመክሮ ጽንሰሐሳብ ሊጠነሰስ አይችልም፡፡

ይህ የእሥራት ውሳኔ ከተወሰነበትና ወደ ማረሚያ ቤት ከተላከ በኋላ በማረሚያ ቤቱ የሚኖረው በሕግ የተወሰነ ቆይታ ሌላው አመክሮን ለመገንዘብ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ነጥብ ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ የተሰጠው የእሥራት ውሳኔ የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ (Determinate or indeterminate sentence)[21] ሲሆን፣ ታራሚው በፍርድ ቤት ውሳኔ

Tobius Mwanza, Parole as a Way to Reduce Overcrowding in Zambian Prisons: A Communicative and Participatory approach, the University of Zambia, 2012, p. 39 available at dspace.unza.zm:8080/xmlui/bitstream/handle/123456789/1800/Tobias, last accessed on July 13 2018)

[17] comprehensive justice system reform program baseline study report, supra note 12, p. 114 እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የታራሚዎች የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ በኢትዮጵያ ማረሚያ ቤቶች መነሻ ክትትል ሪፖርት፣ ሰኔ 2004፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 21 (ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሪፖርት)

[18] Webster's Unabridged International Dictionary, 2nd ed, as cited by Carter H. White, Some Legal Aspects of Parole, 32 J . Crim. L. & Criminology 600 (1941-1942)

[19] Department of Correctional Services. Correctional supervision and parole board manual. Pretoria: Commissioner of Correctional Services, 2004

[20] Mandelko, Neal Louis, "*Parole in theory and practice an evaluation of factors affecting the parole concept,"* thesis, Dissertations, Professional Papers. Paper 9079, 1998፣ p. 6.

[21] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 20-21

ከተጣለበት የእሥራት ቅጣት ውስጥ እንደ ቅደምተከተላቸው በሕግና በአመክሮ ቦርድ ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል የተቀመጠውን ዝቅተኛ የእሥራት መጠን በማረሚያ ቤቱ ውስጥ በመሆን መፈጸም አለበት። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ፣[22] በፈረንሳይና በእስፔን የወንጀል ሕግ መሠረት ማንኛውም ታራሚ በአመክሮ ከእስር ለመለቀቅ ፍርድ ቤቱ ከወሰነው የእሥራት መጠን 2/3ኛ የሚሆነውን በማረሚያ ቤት ሊያሳልፍ ይገደዳል።[23] በዚህ አገላለጽ በፍርድ ቤት ከተወሰነው ቅጣት ውስጥ ታራሚው የአመክሮ ተጠቃሚ ለመሆን በማረሚያ ቤት በመቆየት መፈጸም ያለበት ዝቅተኛ የእሥራት መጠን በፍርድ ከተላለፈው የእሥራት ዘመን ከሦስቱ ሁለት እጁን ነው።

ሆኖም ይህን ያህል የእሥራት ጊዜ በማረሚያ ቤት ማሳለፉ ብቻ የአመክሮ ተጠቃሚ ያደርገዋል ማለት አይቻልም። ይልቁንም በዚህ የቆይታ ጊዜ ያሳየው የባሕርይ መሻሻል ወይም ለውጥ ለአመክሮ መሰጠት እንደ አንድ ተጨማሪና ወሳኝ መስፈርት ሆኖ ያገለግላል። የባሕርይ መሻሻሉ ወይም ለውጡ በሁኔታ ወይም ያለሁኔታ ከማረሚያ ቤት ለመውጣት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው ከፍ ብሎ ለቃሉ ከተሰጡ ፍቺዎች መረዳት ይቻላል። የባሕርይ ለውጡ ተገምግሞ በሁኔታ ወይም ያለ ሁኔታ ከማረሚያ ቤት እንዲወጣና ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ቀሪውን የእሥራት ዘመን እንዲፈጽም ሥልጣን ባለው አካል የተወሰነ እንደሆነ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ሲኖር የሚያሳየውን ባሕርይ ለመከታተልና ለመገምገም ኃላፊነት ያለበት አንድ ባለሙያ ወይም አካል ሊመደብ እንደሚገባም ትርጓሜዎቹ ያሳያሉ።

ከፍ ብሎ ከተመለከቱት ለቃሉ ከተሰጡ ፍቺዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የአመክሮ ጽንሰ-ሐሳብ ይህ ይሁን እንጂ በዚህ ላይ ምርምር ያደረጉ ተመራማሪዎች የሚያነሷቸው ልዩ ልዩ አስተሳሰቦችም አሉ። እነዚህን አሰተሳሰቦች መመልከቱ ጽንሰ ሐሳቡን ይበልጥ ለመረዳት ይረዳል። በመሆኑም አመክሮን ከውል፣ ከችሮታ፣ ከእሥራት ወይም ከጥበቃ፣ ታራሚው መብቱን አሟጦ ከመጠቀሙና በማረሚያ ቤት ቆይታው ካሳየው የባሕርይ መሻሻል (Parens Patriae)[24] አንጻር በመመልከት ባለሙያዎች ጽንሰ ሐሳቡን ያብራራሉ። እነዚህን የፍልስፍና አስተሳሰቦች በአጭር በአጭሩ ማውሳቱ በአመክሮ ጽንሰ ሃሳብ ላይ ያለውን የአስተሳሰብ አድማስ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ያግዛል።

የመስኩ ባለሙያዎች አመክሮን ከውል ወይም ከስምምነት አንጻር ሲተነትኑት አመክሮ በአመክሮ ተጠቃሚውና ሰጭው መንግሥት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ታራሚው ከእስር የሚለቀቅበት አሠራር ነው፣ በማለት ይገልጻሉ።[25] የአመክሮ ተጠቃሚው ከእስር ሲለቀቅ ይህን ስምምነት በመቀበል በስምምነቱ ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመፈጸም ተስማምቷል ለማለት ይቻላል። በዚህ መሠረት ግዴታን የተቀበለ የአመክሮ ተጠቃሚ ሁኔታዎችን አክብሮ በማይገኝበት ጊዜ አመክሮው ቢሰረዝ የስምምነቱ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምክንያቱም በአመክሮ የተለቀቀ ሰው የአመክሮ ቅድመሁኔታዎችን በጣሰ ወይም ባላከበረ ጊዜ ስምምነቱን እንዳፈረሰ ሊቆጠር ስለሚችል ነው።[26]

---

[22] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 202

[23] Champion, D.J..*Probation, parole and community corrections,* 4th edition, Upper Saddle River, NJ: Prentice Hall, 2002, P. 5,

[24] 'The parole system', *University of Pennsylvania law review*, 1971, vol.120, No 282-377, p. 286

[25] Nxumalo, T.E., *Parole supervision: A penological perspective*, MA dissertation, Pretoria University of South Africa, 1997, [unpublished] p 18

[26] ዝኒ ከማሁ

አመክሮን አስመልክቶ የሚቀርበው ሁለተኛው አስተሳሰብ አመክሮ በመንግሥት በጎ ፈቃድ ወይም ችሮታ ላይ ተመስርቶ ታራሚው ከእስር የሚለቀቅበት እንጂ እንደ መብት የሚጠየቅ ጉዳይ አለመሆኑን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡[27] በዚህ እይታ መሠረት አመክሮ መንግሥት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምነውን ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ታራሚውን ከእስር የሚለቅበትና የአመክሮ ተጠቃሚው ቅድመ ሁኔታዎችን ጥሶ በሚገኝበት ጊዜ ያለምንም ሥነ ሥርዓት ወደ እስር የሚመልስበት የመንግሥትን በጎ ፈቃድ ብቻ መሠረት ያደረገ አሰራር ነው፡፡[28] በመሆኑም የአመክሮ ተጠቃሚው እንደመብት የሚጠይቀው ሳይሆን የመንግሥትን መሀሪነት ወይም ይቅር ባይነት መሠረት በማድረግ እንዲለቀቅ የሚማጸንበት አሠራር ነው ብለው የመስኩ ባለሙያዎች ይሞግታሉ፡፡[29]

የባለሙያዎች ሦሥተኛው አስተሳሰብ አመክሮ ተጠቃሚውን በጥበቃ ወይም በእስር ላይ ካለ ታራሚ ጋር የሚያመሳስል ነው፡፡[30] በዚህ የአስተሳሰብ ጎራ የሚነሳው በአመክሮ የተለቀቀ ታራሚ በቁጥጥር ወይም በክትትል ሥር ያለና ሁኔታውም የእሥራቱ አካል እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡[31] የአመክሮ ቦርድ ወይም ሌላ ሥልጣን የተሰጠው አካል በአመክሮ የተለቀቁ ታራሚዎች ላይ በእስር እንዳሉት ፍርደኞች ሁሉ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግና የባሕርያቸውን መልካምነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡[32] በክትትሉ በአመክሮ የተለቀቁ ሰዎች የተጣለባቸውን ገደብ ተላልፈው ወይም ሌላ ወንጀል ፈጽመው የተገኙ እንደሆነ ከእስር እንዳመለጡ ታራሚዎች ተቆጥረው ያለምንም የፍርድ ሂደት ወደነበሩበት ማረሚያ ቤት እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡[33] ይህም አመክሮ የቀድሞው እሥራት ቅጥያ መሆኑን በግልፅ ያመላክታል፡፡

ከአመክሮ ጽንሰ ሐሳብ ጋር የሚነሳው ሌላው አስተሳሰብ የስነ ሥርዓት መብትን የሚመለከት ነው፡፡ ከላይ አመክሮን ከእሥራት ጋር በማስተሳሰር ለማብራራት የተሞከረበት አስተሳሰብ አመክሮ ተጠቃሚው የተጣለበትን ገደብ ተላልፎ ወይም አዲስ ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ የአመክሮ ተጠቃሚ ያለምንም ተጨማሪ ስነሥርዓት ወደ ማረሚያ ቤት እንደሚመለስ በአንክሮ ይገልጻል፡፡[34] ይህ አስተሳሰብ በፍርድ ቤት የክርክር ሂደት አልፎ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገባ የተደረገ ታራሚ በማረሚያ ቤትም ይሁን በአመክሮ ጊዜ ሊያነሳ የሚችለው የስነ ሥርዓት (due process right) መብት እንደሌለ ያስገነዝባል፡፡[35] ምክንያቱም ታራሚው የዚህ አይነቱን መብት የቅጣት ውሳኔ እስከ ተሰጠበት ባለው የክርክር ሂደት ሙሉ በሙሉ ስለተጠቀመበት ነው፡፡[36] ሥለሆነም የአመክሮ ገደብን በመተላለፉ ቀሪውን የእሥራት ጊዜ

---

[27] The parole system, supra note 24.

[28] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 287.

[29] ዝኒከማሁ

[30] Clear, T.R. & Dammer, H.R, *The offender in the community,* Second edition. Belmont: Wadsworth. 2003, p.347

[31] Francois Christiaan, *The Parole Process from a South African Perspective*, masters thesis, University Of South Africa , November 2008, p. 36 available http://uir.unisa.ac.za/bitstream/handle/10500/1320/dissertation.pdf?sequence=1, last accessed on 10 August 2017)

[32] Clear, T.R. & Dammer, H.R, supra note 30

[33] ዝኒ ከማሁ

[34] The parole system, supra note 23, p. 288

[35] ዝኒ ከማሁ

[36] ዝኒ ከማሁ

ታራሚው ወደማረሚያ ቤት ተመልሶ እንዲፈጽም በአመክሮ ቦርድ ወይም ሌላ ሥልጣን ባለው አካል ሲወሰን ሊነሳ የሚችል የስነሥርዓት መብት ሊኖር አይችልም፡፡

በመጨረሻ የሚነሳው ነጥብ አመክሮ ታራሚው በማረሚያ ቤት ቆይታው የሚያሳየው የባሕርይ ማሻሻል (Parens Patriae) ሲሆን፣ ይህ አስተሳሰብ አመክሮ ለማንኛውም ታራሚ የሚሰጥ ሳይሆን በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የባሕርይ መሻሻል እንዳሳዩ በአመክሮ ቦርዱ ለታመነባቸው ታራሚዎች ብቻ የሚሰጥ ነው፡፡ የአመክሮ ቦርድ ይህን መሠረት አድርጎ አመክሮ እንዲሰጥ በሚያስተላልፈው የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ቤት ሊከለስ አይገባውም[37]፤ የሚል አስተሳሰብን የሚያስተጋባ ነው፡፡

ከላይ የተቃኙት የተለያዩ ባለሙያዎች አተያዮች የአመክሮን ባሕርያት መሠረት በማድረግ ጽንሰሐሳቡን ለማብራራት የሚያግዙ ይሁኑ እንጂ በየራሳቸው ሲታዩ ህፀፅ አልባ ባለመሆናቸው እያንዳንዳቸው ለትችት የተጋለጡ ናቸው፡፡ አስተሳሰቦቹን በተመለከተም ጸሕፍት በነዚሁ አስተሳሰቦች መካከል የሐሳብ ተቃርኖ እንዳለ ያሳያሉ፡፡[38] ሌላው ቀርቶ በእያንዳንዱ አስተሳሰብ ውስጥ የሐሳብ አለመጣጣም እንደሚስተዋል[39] በማንሳት የአስተሳሰቦቹን ተቀባይነት ጥያቄ ውስጥ ይጥሉታል፡፡

በአጠቃላይ የአመክሮ ጽንሰሃሳብ በዚህ ጥናት ውስጥ ከተብራሩት መሠረተ ሐሳቦች የተዋቀረና በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ አልፈው የባሕርይ መሻሻል ያሳዩ ታራሚዎችን ወደ ማህበረሰቡ እንዲቀላቀሉ በማድረግ የታራሚዎችን፣ የህዝብንና የመንግሥትን ጥቅም ለማስከበር የሚያገለግል ሥርዓት ነው፡፡

## 2. የአመክሮ ታሪካዊ ዳራ

የአመክሮ ታሪካዊ ዳራ ሲቃኝ ወደ ጥንቱ የሙሴና የሀሞራቢ የሕግ ሥርዓት ያመራናል፡፡ በሙሴ ዘመን በወቅቱ የነበረውን ሕግ በመተላለፍ ወንጀል ወይም ኀጢአት የፈጸመ ሰው ከሚኖርበት ግዛት ወይም አካባቢ በመሸሽ ተሰድዶ በሌላ አካባቢ እንደ ንጹህ ሰው ተቆጥሮ በነጻነት እንዲኖር ይደረግ ነበር፡፡[40] በተሰደደበት ግዛት ብቻ እንዲንቀሳቀስና በነጻነት እንዲኖር ሲፈቀድለት፣ ከዚያ ግዛት ክልል ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ውሳኔውን እንደተላለፈ ተቆጥሮ ባላጋራዎቹ በተገኘበት እርምጃ እንዲወስዱበት ለምሳሌም በሰው መግደል ወንጀል ተበይኖበት ከሆነ ግድያ እንዲፈጸምበት ይደረግ ነበረ፡፡[41]

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በወቅቱ እጅግ በጣም ገናና የነበረችው እንግሊዝ በግዛቷ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችን በወቅቱ ቅኝ ግዛቶቿ ወደነበሩት አሜሪካ፣ በኋላም ወደ አውስትራሊያና የአፍሪካ ሀገሮች እንዲጓዙ ታደርግ ነበረ፡፡[42] በሌላ አነጋገር በእንግሊዝ ሕግ ወንጀለኛ ተብለው የተፈረደባቸው ታራሚዎች ከላይ ወደ ተጠቀሱት ሀገሮች ተወስደው በልዩልዩ ሥራዎች ላይ በአገልጋይነት እንዲሰማሩ ይደረግ ነበር፡፡ በተለይ በ18ኛው ክፍለዘመን

---

[37] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 289

[38] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 289-291

[39] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 291-296፤ ሆኖም የዚህ ጥናት አላማ እነዚህን ፍልስፍናዎች ወይም አስተሳሰቦች መመርመር ባለመሆኑ ዝርዝሩን አንባቢያን በዚሁ በግርጌ ማስታዎሻ ላይ የተመለከተውን ጽሑፍና ሌሎችንም ፈልጎ በማንበብ ይበልጥ እንዲገነዘቡት የጥናቱ አቅራቢዎች ይመክራሉ፡፡

[40] Mandelko, Neal Louis, supra note 20

[41] ዝኒ ከማሁ

[42] Frederick a. Moran, ( Chairman, New York State Board of Parole), the Origins of Parole, http://heinonline.org, last accessed on 8 July 20-17), pp. 71-73

አሜሪካ የራሷን ነጻ መንግሥት ከመሰረተች በኋላ እንግሊዝ አውስትራሊያን እንደ አማራጭ የእስረኞች መጠበቂያ አድርጋ መገልገል ብትጀምርም የአውስትራሊያ ቀደምት ሰፋሪ የነበሩ እስረኞች በእንግሊዝ ላይ የመሬት አጠቃቀምን ምክንያት በማድረግ ተቃውሞ በማንሳታቸው አመክሮ እንደ ችግር መፍቻ ሆኖ እንዲታሰብ ሁኔታው አስገድዷል።[43] በዚህ መሠረት በአውስትራሊያ እንዲሰፍሩ ሲደረጉ የነበሩ ታራሚዎች ለተወሰነ ጊዜ ለቀደሙት ታራሚዎች ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ያሳዩት የባሕርይ ለውጥ ግምት ውስጥ ገብቶ መሬት ተሰጥቷቸው ለራሳቸው እየሰሩ እንዲተዳደሩ መደረግ ጀመረ።[44] ይህም አመክሮ በሁኔታ ወይም ያለሁኔታ ለመስጠት ታሪካዊ መነሻ ሆኖ በዘመናዊ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽንሰ ሐሳቡ በ19ኛው ክፍለዘመን ዳብሮ መተግበር እንደጀመረ ይነገራል።[45]

ይህንን ተከትሎ ወደ አውስትራሊያና ሌሎች ግዛቶች ለሚላኩ እስረኞች በፍርድ ቤት የተወሰነባቸው ቅጣት በይቅርታ መልክ እንዲቀንስላቸው ለማድረግ እ.አ.አ በ1790ዎቹ ሕግ ወጥቶ ተግባራዊ ሆኗል። በዚህ መሠረት እ.አ.አ ከ1811 ጀምሮ የባሕርይ መሻሻል፣ በቆይታቸው መልካም ሥራን ሠርተው እውቅናን ያገኙና ጋብቻን ፈጽመው ለትዳር ብቁና ዝግጁ ሆነው የተገኙ እስረኞች ፍርዳቸውን ሳይጨርሱ ሙሉ በሙሉ ከገደብ ነጻ ሆነው ከእሥራት እንዲለቀቁ መደረጉ አመክሮ በዘመናዊ መንገድ መሠጠት መጀመሩን አመላክቷል።[46] በተለይም እ.አ.አ በ1830 እና 1835 በፈረንሳይና በእስፔን እንደቅደምተከተላቸው አመክሮ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ገሃድ ሆኗል።[47] በእነዚህ ሀገሮች በፍርድ ቤት ከተወሰነው ቅጣት 2/3ኛውን በማረሚያ ቤት ሲቆይ፣ በዚህ ወቅትም ትምህርትና የሙያ ሥልጠና ከተከታተለ እንዲሁም የባሕርይ መሻሻል በማሳየት ለተሻለ ሥራ ከተነሳሳ 1/3ኛውን የእሥራት ጊዜ ከማረሚያ ቤት ውጭ ሆኖ እንዲፈጽም መደረግ ተጀምሯል።[48]

ለአመክሮ አሰጣጥ እንደ ቅድመሁኔታ ሆነው ከሚያገለግሉት መስፈርቶች አንዱ የሆነውን የባሕርይ መሻሻል ለመለካት በወቅቱ አስቸግሮ ስለነበረ እ.አ.አ በ1840 የኖርፎክ ደሴት ገዥ የነበረው አሌክሳንዶር ማኮኖቼ ታራሚዎች በአመክሮ ለመለቀቅ በእስር መቆየት ያለባቸው ጊዜ በሚሰሩት ሥራና በሚያሳዩት የባሕርይ ለውጥ መመዘን እንዳለበት ሐሳብ አቅርቧል። ምዘናውም ታራሚው በየቀኑ ለሚሰራው ሥራ ነጥብ በመስጠት መደረግ እንዳለበት ግለሰቡ ተጨማሪ ሐሳብ ሰንዝሯል።[49] ይህም በዘመናዊ አመክሮ አሰጣጥ ተቀባይነትን አግኝቶ ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ ሀገሮች እየተሰራበት ይገኛል።

## 3. የአመክሮ አስፈላጊነት

የአመክሮ አስፈላጊነት የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ዓላማ ከሆነው የማህበረሰብ ወይም የህዝብ ደህንነት የሚመነጭ ነው።[50] ታራሚዎች ይህንን ደህንነት የሚያደፈርስ ወንጀል

---

[43] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 76

[44] Mandelko, Neal Louis, supra note 20, p. 5

[45] ዝኒ ከማሁ

[46] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 13

[47] Champion, D.J, *Probation, parole and community corrections*, 4th edition, upper Saddle River, NJ: Prentice Hall, 2002, p. 260

[48] ዝኒ ከማሁ

[49] ዝኒ ከማሁ

[50] Cromwell, P.F. & Del Carmen, R.V, Community-*based corrections*, 4th edition, Belmont: Wadsworth, 1999, P. 2.

በመፈጸማቸው ተፈርዶባቸው በእስር ከቆዩ በ ኋላ ሲለቀቁ ከመሰል የወንጀል ባሕርያቸው ስለ መታረማቸው ማስረጃ ያሻል።[51] በሌላ አነጋገር ታራሚዎች በአመክሮ ከወጡ በኃላ ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጽሙ አስፈላጊው ቅድመጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል። ለዚህም ሲባል ታራሚው ከማረሚያ ቤት ሲለቀቅ የሚያሟላቸው መስፈርቶች አብዛኛዎቹ ከባሕርይ መለወጥ ወይም መስተካከል ጋር የተያያዙ ናቸው።[52] ታራሚው እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ ከእስር እንዲለቀቅና ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ እንዲኖር ሲደረግ ኃላፊነት የሚሰማውና ለሕግ ተገዥ የሆነ መልካም ዜጋ እንዲሆን ታምኖበት ነው።[53] ይሁን እንጂ ታራሚው በአመክሮ ከተለቀቀ በኂላ ለዚህ ባሕርይው ዋስትና ይሆን ዘንድ የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል።[54] የክትትል ሥርዓቶቹም ተቆጣጣሪ መመደብ፣ ገደብ መጣልና ልዩልዩ የቁጥጥር ዘዴዎችን በመጠቀም ግለሰቡ ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽም ማገዝ ሲሆኑ፣ እነዚህን ተላልፎ ከተገኘ አመክሮውን በማንሳት ወደ ነበረበት ማረሚያ ቤት እንዲገባ ማድረግ ነው።[55] በዚህ መንገድ አመክሮን በመፈጸም የማህበረሰቡን ደህንነት መጠበቅና ታራሚውንም አመክሮን በመጠቀም መልካም ዜጋ እንዲሆን ያስችላል።[56]

ሌላው አመክሮ ሲሰጥ ግምት ውስጥ የሚገባው ከአመክሮ ተጠቃሚው ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ የሚታየው የአመክሮ አስፈላጊነት ታራሚው ባሕርይውን እንዲያሻሽል፣ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ እንዲኖርና የግል ተበዳዮችንና ማህበረሰቡን በድርጊቱ ተጸጽቶ እንዲክስ ማስቻል ነው።[57] ታራሚን በአመክሮ ለመልቀቅ ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች አንዱ የባሕርይ መሻሻል ሲሆን፣ ይህ የወንጀል ሕግ ዋነኛና ቀዳሚ የወንጀል ቅጣት ዓላማ እንደሆነ ይታወቃል።[58] ታራሚዎች በአመክሮ ከእስር በሚለቀቁበት ጊዜ ይህ ዓላማ በትክክል ስለመሳካቱ መመዘን እንዳለበት በዙሪያው የመስኩ ጠበብት ይስማማሉ።[59] የብዙ ሀገሮች የወንጀል ሕግጋትም የወንጀለኛውን የባሕርይ መሻሻል እንደዋና ቅድመሁኔታ አድርገው ይደነግጋሉ።[60] ስለሆነም በአመክሮ አንድን ታራሚ ከእሥራት ለመልቀቅ የባሕርይ ለውጥ ማምጣቱንና ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀል እንደ መልካም ዜጋ ለመኖር የሚያስችለውን መልካም ባሕርይ የተላበሰ መሆኑን ማረጋገጥ በአመክሮ አሠራር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መስፈርት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

---

[51] Champion, D.J, supra note 47

[52] ዝኒ ከማሁ

[53] Cromwell, P.F. & Del Carmen, R.V, supra Note 50

[54] Champion, D.J, supra note 47

[55] Clear, T.R. & Dammer, H.R, supra Note 30

[56] Cromwell, P.F. & Del Carmen, R.V, supra Note 50

[57] Stevens, D.J, *Community corrections: An applied approach,* Upper Saddle River, NJ: Prentice Hall, 2006, p. 291

[58] Thom Brooks, *Punishment,* Routledge, 2012, pp.51-52

[59] ዝኒ ከማሁ

[60] ለምሳሌ የአሜሪካ የተለያዩ ክልል መንግሥታት የወንጀል ሕግጋት ለአመክሮ የባሕርይ መሻሻል ዋና መስፈርት እንደሆን ይደነግጋሉ፤ ለተጨማሪ ማብራሪያ ይህን ጽሑፍ ይመልከቷል።

Prison Law Office, The Parolee Rights Handbook (Updated August 2013) available at www.prisonlaw.com, last accessed on July 14 2018.

የተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች ሕግጋትም ተመሳሳይ የአመክሮ ቅድመሁኔታን እንደያዙ የበለጠ ለመረዳት የሚከተለውን ጽሑፍ ይመልከቷል፤ *Pierre V. Tournier*, Systems of Conditional Release ( Parole) in the Member States of the Council of Europe, A New French Journal, vol 1, 2004, available at https://journals.openedition.org/champpenal/378, last accessed on July 14 2018.

ከላይ የተመለከተውን የባሕርይ ለውጥ መላበሱ የታመነበት ታራሚ ከእስር ሲለቀቅ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎና ተስማምቶ ለመኖር እንደማይቸገር በዘርፉ የተካኑ የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡[61] ምክንያቱም በማረሚያ ቤት ቆይታው ባገኘው ትምህርትና ልዩልዩ ሥልጠናዎች የነበረውን የወንጀል ባሕርይ በማስወገድ መልካም ጸባይና ለሕግ ተገዥ እንዲሆን የሚያስችለው የባሕርይ ለውጥ ስለሚያመጣ ነው፡፡ በተጨማሪም አመክሮ ለረጅም ጊዜ ከማህበረሰቡ ተገልሎ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ከተሰጠው የፍርድ መጠን ላይ በከፊል ተቀንሶ የነበረበትን ማህበረሰብ ወግና ባህል ሳይረሳና ብቸኝነትን ሳይላመድ የመጨረሻው የእሥራት ዘመን ከመድረሱ በፊት ከእስር ወጥቶ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር ስለሚያስችለው ነው፡፡[62]

ሌላው ከግለሰቡ ባሕርይ ጋር የተያያዘው የአመክሮ አመክንዮ በአመክሮ ከእስር ተለቅቆ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ በሚኖርበት ጊዜ በፈጸመው ድርጊት ተጸጽቶ የወንጀል ድርጊቱ ሰለባ የሆነውን ግለሰብና የበደለውን ማህበረሰብ ለመካስ የሚያስችለው የባሕርይ ለውጥ ማምጣቱ ነው፡፡[63]

በሦሥተኛ ደረጃ የሚነሳው የአመክሮ አስፈላጊነት ታራሚው በማረሚያ ቤት ሳለ የአመክሮ ተጠቃሚ ለመሆን ሲል ለማረሚያ ቤቱ ሕግና ደንብ የሚኖረው ተገዥነትና ባሕርይውን ለማሻሻል የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡[64] በተለይ ታራሚው በማረሚያ ቤት ቆይታው በሚያሳየው ብልሹ ስነ-ምግባር የተነሳ አመክሮ አንድ ጊዜ ከተከለከለ በሚቀጥለው እድል ለመጠቀም የሚያደርገው የባሕርይ ማሻሻል እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡[65]

አመክሮ ከላይ ከተጠቀሱት ጠቀሜታዎች በተጨማሪ የቅጣት ዓላማም አለው፡፡[66] በአመክሮ የሚለቀቅ ሰው ሙሉ ነጻነት ሳይሰጠው በገደብና በቁጥጥር ሥር እንዲንቀሳቀስ ተደርጎ የቀረውን የእሥራት ዘመን እንዲፈጽምና ይህንን ሳያከብር ከቀረም አመክሮው ተነስቶ ወደማረሚያ ቤት እንዲገባ የሚደረገው ቅጣቱን እንዲፈጽምና መልካም ዜጋ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡[67] በመሆኑም አመክሮ ታራሚውን ከቅጣት ሙሉ በሙሉ ነጻ እንደሆነ እንዲሰማው አያስችለውም፡፡[68] በማረሚያ ቤት ውስጥ የሚፈጠረውን የእስረኞችን መጨናነቅና የመንግሥትን ወጭ መቀነስም የአመክሮ ሌላው አስፈላጊነት እንደሆነ ይታመናል፡፡[69]

## 4. አመክሮ በተመረጡ ጥቂት ሀገሮች

አመክሮ በብዙ ሀገሮች የሕግ ማእቀፍ ተበጅቶለትና ሥርዓት ተዘርግቶለት እየተከናወነ ያለ የሕግ አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያን አመክሮ አሠጣጥ ሕግና አፈጻጸም ከማውሳት

[61] Keith Spencer, 'community Reintegration',2006, pp. 2 &3, http://heinonline.org, last accessed on 22 July 2017),

[62] ዝኒ ከማሁ

[63] Stevens, D.J., supra note 57

[64] Proctor, J.L. & Pease, M. 'Parole as institutional control: A test of specific deterrence and offender misconduct', *The Prison Journal*, 80(1), March 2000, pp. 39-55.

[65] ዝኒ ከማሁ

[66] Clear, T.R. & Dammer, H.R., supra note 30, p. 21

[67] ዝኒከማሁ

[68] ዝኒ ከማሁ

[69] ዝኒ ከማሁ

በፊት በዘርፉ ጥሩ ልምድ ያላቸውን ሀገሮች መርጦ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥናት ዓላማም በዘርፉ የዘመነ ሕግና የዳበረ ልምድ ያላቸው ሀገሮች ተመርጠው አመክሮ በእነዚህ ሀገሮች ምን መልክ እንዳለው ቀጥሎ ተቃኝቷል፡፡

### 4.1 ካናዳ

ካናዳ አመክሮን የሚመለከት ብሄራዊ ቦርድ አቋቁማ በአመክሮ መለቀቅ ያለባቸውን እስረኞች በየጊዜው የአመክሮ ተጠቃሚ ከሚያደርጉ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ የሀገሪቱ የአመክሮ ብሄራዊ ቦርድ በአመክሮ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለማስተላለፍ ገለልተኛ፣ ነጻና ምክንያታዊ ሆኖ ይሠራል፡፡[70] በዚህ መልኩ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የማህበረሰቡንና የወንጀል ሰለባዎችን ደህንነት መጠበቅ፣ የፍትህ አካላትን በሂደቱ ማሳተፍ፣ የአመክሮ ተጠቃሚው መቼና ለምን ከእስር እንደሚለቀቅ እንዲሁም ይህን ተከትሎ ያለበትን ግዴታና መብት የማሳወቅና ሌሎችንም መርሆዎች መሠረት ያደርጋል፡፡[71] እነዚህን መርሆዎች መሠረት በማድረግ አመክሮ ተጠቃሚዎችን ለመለየት ብሄራዊ ቦርዱ የሚከተሉትን ቅድመሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡[72]

- የተፈጸመው የወንጀል አይነት፣
- የታራሚው የቀደመ የወንጀል ባሕርይ፣
- በቅድመአመክሮ ያከናወናቸው ተግባራት፣
- የደባል ሱስ ተገዥ መሆን አለመሆኑ፣
- ወደፊት ለወንጀል ያጋልጠዋል ተብሎ የሚታመን የአእምሮ ሁኔታ መኖር አለመኖሩ፣
- የታራሚውን የሥራና ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚመለከት መረጃ፣
- ታራሚውን በሚመለከት የቀረቡ ስነልቦናተኮር መግለጫዎች፣
- የፍትህ አካላት ባለሙያዎችና የወንጀል ሰለባዎችን አስተያየት፣

የካናዳ አመክሮ ብሄራዊ ቦርድ እነዚህን ቅድመ-ሁኔታዎች በሕግ አስፍሮ መሟላታቸውን እያረጋገጠ ታራሚዎች በአመክሮ እንዲለቀቁ ማድረጉ የተለመደ አሠራር ነው፡፡[73] መስፈርቶቹን አሟልተው ለተገኙ ታራሚዎች ሦስት አይነት የአመክሮ መርሃ-ግብሮች በሀገሪቱ ይተገበራሉ፡፡ የመጀመሪያው ታራሚው ቀን ቀን እየተለቀቀ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ሲሰራ ውሎ አዳሩን ማረሚያ ቤት የሚያሳልፍበት ነው፡፡[74] የዚህ ዓላማ ታራሚው በማረሚያ ቤት ቆይታው ያሳየውን የባሕርይ ለውጥ ለመፈተሽና ለሙሉ አመክሮ ያለውን ዝግጁነት ለማረጋገጥ ነው፡፡[75] በዚህ ሙከራ የባሕርይ ለውጥ እንዳመጣ ከተረጋገጠ ታራሚው የሙሉ አመክሮ ተጠቃሚ እንዲሆን ይወሰንለታል፡፡ ሁለተኛው የባሕርይ ለውጥ ያመጡትን ታራሚዎች ሙሉ በሙሉ ከማረሚያ ቤቱ አስተዳደር በማውጣት የቀረውን የእሥራት ዘመን ወደማህበረሰቡ በመመለስ መደበኛ ኑሯቸውን እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው

---

[70] Parole board of Canada, available at https://www.canada.ca/en/parole-board.html, last accessed 02 July 2018.

[71] ዝኒ ከማሁ

[72] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 109

[73] ዝኒ ከማሁ

[74] Dunberry, O.G., *Parole in Canada: Community safety through effective reintegration of offenders*, 2004,available at http://www.isrcl.org/Papers/2004/ Dunberry.pdf last accessed 20 September 2008.

[75] ዝኒ ከማሁ

ነው፡፡[76] ይሁን እንጂ ታራሚዎቹ በአመክሮ እስካሉ ድረስ የተጣለባቸውን ገደብና ቁጥጥር እንዲያከብሩ ይገደዳሉ፡፡[77] ሦሥተኛውና የመጨረሻው ታራሚው በፍርድ ቤቱ ከተጣለበት ውሳኔ በሕግ የተወሰነውን 2/3 ጊዜ በማረሚያ ቤቱ ከቆየና መስፈርቶቹን ካሟላ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ መደበኛ ኑሮውን እንዲመራ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡[78]

ካናዳ አመክሮን ከፍ ብሎ በተገለጸው መልኩ ለረዥም ዘመናት ስትሰጥ የቆየችና እየሰጠች ያለች አገር ስትሆን፣ አመክሮን ለመጀመሪያ ጊዜ የሕግ ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ መስጠት የጀመረችው እ.ኤ.አ በ1899 እንደሆነ ይነገራል፡፡[79] የዚህን ሕግ መውጣት ተከትሎ በርካታ ታራሚዎች በሁኔታ ወይም ያለሁኔታ የአመክሮ ተጠቃሚ መሆን በመጀመራቸው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሲኖሩ የሚያሳዩትን ባሕርይ ለመገምገምና ከሚያጋጥማቸው ችግር እንዲላቀቁ የሚያግዛቸው የክትትል ባለሙያ እንዲኖር ተደርጓል፡፡[80] ባለሙያው በአመክሮ የሚለቀቁትን ታራሚዎች ሁኔታ ከማረሚያ ቤት ጀምሮ ክትትልን እያደረገ ድጋሜ ወደ ወንጀል ድርጊት እንዳይገቡ አስፈላጊውን የጥንቃቄ ሥራ ያከናውናል፡፡[81] ባለሙያው በአመክሮ ቦርድ ሥር ተደራጅቶ ይህንን መሰል ተግባር ማከናወኑ ለአመክሮ መርሀ-ግብሮቹ ውጤታማነት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታመናል፡፡[82]

በአጠቃላይ የካናዳው ብሄራዊ አመክሮ ቦርድ ከማረሚያ ቤቱ አስተዳደርና ቁጥጥር ገለልተኛና ነጻ በመሆን ከፍ ብሎ የተመለከቱትን መርሆዎች መሠረት አድርጎ የቅድመ-ሁኔታዎችን መሟላትና አለመሟላት በአግባቡ እየመዘነ ታራሚዎች የአመክሮ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ውሳኔ በማስተላለፍ በማረሚያ ቤቶች በኩል ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በሥሩ የክትትል ባለሙያ እንዲኖር በማድረግ የአመክሮ ተጠቃሚዎች ባሕርይ መሻሻልን ከማረሚያ ቤት ጀምሮ በመከታተል ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሲኖሩ የሚያጋጥማቸውን ችግር እንዲፈቱ የማስቻል ሥራ ያከናውናል፡፡

### 4.2 አሜሪካ (United Sates of America/USA)

አመክሮ በአሜሪካ እ.ኤ.አ በ1850ዎቹ በሚችጋን ግዛት ይጀመር እንጂ በ20ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ በብዙዎቹ የአሜሪካ ግዛቶች መሰጠት ተጀምሯል፡፡[83] እ.ኤ.አ በ1930 ሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች አመክሮን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አካል በማድረግ አፈጻጸሙን በተደራጀ መልኩ ለመከወን የሚያስችል የአመክሮ ቦርድ በሁሉም ግዛቶች ተቋቁሟል፡፡[84] ይኸው አሰራር በፌዴራልና በሁሉም የክልል መንግሥታት እ.ኤ.አ እስከ1975 ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡[85] በአሜሪካ የአመክሮ አሠጣጥ ከግዛት ግዛት ወይም ከክልል ክልል

[76] ዝኒ ከማሁ

[77] ዝኒ ከማሁ

[78] ዝኒ ከማሁ

[79] A. Keith Bottomley, 'Parole in Transition: A Comparative Study of Origins, Developments, and Prospects for the 1990s,' *Crime and Justice*,Vol. 12, The University of Chicago Press, 1990, pp. 334-336

[80] ዝኒ ከማሁ

[81] ዝኒ ከማሁ

[82] ዝኒ ከማሁ

[83] A. Keith Bottomley, supra note 79, p. 322

[84] ዝኒ ከማሁ

[85] ዝኒ ከማሁ

የተለያየ ይሁን እንጂ በጥቅሉ ሲታይ አመክሮ በሁለት አይነት መዋቅር ይፈጸማል፡፡ በማረሚያ ቤቶች ድፓርቲሜንት የሚሰጠው የአመክሮ አይነት (a consolidation model) እና እንደ ካናዳና አፍሪካዊቷ ናሚቢያ አይነት ራሱን ችሎ በሀገርአቀፍ ደረጃ ተዋቅሮ እየሰራ ያለ የአመክሮ ቦርድ (autonomous model) ናቸው፡፡[86] ሁለቱም የአመክሮ ቦርድ አወቃቀር አይነቶች ግን ተመሳሳይ ዓላማና መስፈርት ባለው መልኩ አመክሮን በአሜሪካ ግዛቶች ያከናውናሉ፡፡[87] ለዚህ ጥናት ዓላማ በአሜሪካ የፌዴራል መንግሥት ሥራ ላይ ባለው ሞዴል የወንጀል ሕግ ሥር የተደነገጉትን መሪ የአመክሮ አሠጣጥ መስፈርቶች መመልከቱ በቂ ይሆናል፡፡ በዚህ ሕግ የተመለከቱ መሪ የአመክሮ መስፈርቶች በርከት ያሉ ሲሆኑ፣ ዋና ዋናዎቹም፤ በአመክሮ ተቋም ባለሙያ ጥናት የሚቀርብ የታራሚው ሰብዕና፣ ማህበራዊ ሁኔታ፣ ከተቋሙ ጋር ያለው ቀረቤታና ሌሎችንም የግል ሁኔታዎች የተመለከተ መረጃ፣ የቀደመ የወንጀል፣ የገደብና አመክሮን የሚመለከት መረጃ፣ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ቅድመውሳኔ አስተያየት፣ በቅጣት አወሳሰን ወቅት አመክሮን አስመልክቶ በዳኛ ወይም በዓቃቤ ሕግ የተሰጠ አስተያየት፣ የአመክሮ ተጠቃሚውን አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነልቦናዊ ቁመናውን በተመለከተ ከጤና ተቋማት የተገኘ መረጃና በታራሚው፣ በጠበቃው፣ በወንጀል ሰለባው ወይም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው በኩል የቀረበ አግባብነት ያለው መረጃ እንዲሁም ሌሎች ናቸው፡፡[88]

ከላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በመመዘን የሚሰጠው አመክሮ የሚከተሉትን ስድስት የተለያዩ እሴቶች መሠረት ማድረግ እንደሚገባው ይታመናል፡፡ እነዚህም፤ ለታራሚው በወንጀል ሕግ የተሰጠውን በአመክሮ የመለቀቅ እድል፣ ታራሚው በአመክሮ ከመለቀቁ በፊት በእስር የሚቆይበት ጊዜ፣ ታራሚው በማረሚያ ቤት ቆይታው ያሳየውን የባሕርይ ለውጥ፣ የማህበረሰቡን ደህንነት ግምት ውስጥ በማስገባት በታራሚው ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የማህበረሰቡን ጥቅምና ከታራሚው የሚጠብቀውን ሃላፊነት መሠረት ያደረገ የአመክሮ ውሳኔ መስጠትና የአመክሮ ተጠቃሚው ውሳኔውን ተከትሎ የሚሰጠው ምላሽ (reactions) ናቸው፡፡[89]

በአጠቃላይ በአሜሪካ ልየልዩ ግዛቶች የፌዴራል መንግሥቱን ጨምሮ አመክሮ በተለያየ መልኩ የሚሰጥ ቢሆንም ከፍ ብሎ የተመለከቱ መስፈርቶችና እሴቶች መሠረት ሆነው ያገለግላሉ፡፡

## 5. አመክሮ በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍና በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት ያለው አፈጻጸም

በቀደሙት የጥናቱ ክፍሎች ስለአመክሮ በጠቅላላውና የዘመነ ሕግና አሰራር ባላቸው ሀገሮች አመክሮ ያለውን ይዘት ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ አመክሮ በኢትዮጵያ በፌዴራል መንግሥትና በአማራ ብሄራዊ ክልል የወንጀል ፍትህ አስተዳደር በጠቅላላው፤ በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት በተለይ ምን እንደሚመስል፣ የሚስተዋሉ የሕግና የአፈጻጸም ክፍተቶች ምን እንደሆኑ በመለየት መፍትሄ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ሐሳቦችን ለማመላከት ጥረት ተደርጓል፡፡

---

[86] Clear, T.R. & Dammer, H.R,supra note 30, p. 369

[87] ዝኒ ከማሁ

[88] The Parole System, supra note 24, p. 302

[89] Champion, D.J. supra note 23, P. 324

### 5.1 አመክሮ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ

የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አመክሮን በተመለከተ ከአንቀጽ 201 እስከአንቀጽ 207 ባሉ ድንጋጌዎች መሠረታዊ መርሆዎችን ይዟል፡፡ በዚህ መሠረት አመክሮ አንድ ታራሚ በፍርድ ቤት ከተወሰነበት ነጻነትን ከሚያሳጣ የቅጣት ውሳኔ ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ከሦስቱ እጅ ሁለቱን እጅ የፈጸመ እንደሆነ፣ ቅጣቱ የእድሜ ልክ እሥራት ከሆነ ቢያንስ 20 ዓመት በእስር ከቆየና በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ቀሪውን ቅጣት ከማረሚያ ቤት ውጭ ሆኖ እንዲፈጽም ከእስር የሚለቀቅበት መንገድ ነው፡፡[90] አመክሮ የሚሰጥበት ምክንያት ታራሚው ጠባዩን እንዲያሻሽልና ወደ ማህበረሰቡ ተመልሶ መደበኛውን ማህበራዊ ሕይወት በአግባቡ እንዲኖር ለማስቻል እንደሆነ ከዚሁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገርግን አመክሮ ይህንን ውጤት ማስገኘት እንደማይችል ከታመነ ታራሚው በዚህ መልኩ ከማረሚያ ቤት ወጥቶ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀል መደረግ እንደሌለበት የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ያስገነዝባል፡፡[91]

በአመክሮ የሚለቀቀው ታራሚ ከላይ የተመለከተውን ባሕርይ የተላበሰ መሆኑን ለመለካት ሕጉ መሟላት ያለባቸውን ቅድመሁኔታዎች በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ቅድመ-ሁኔታዎቹም፤ በፍርድ ቤት ከተላለፈው ቅጣት 2/3ኛውን መፈጸም፣ ከተበዳይ ጋር በተደረገ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን ካሳ መክፈል፣ በማረሚያ ቤት ቆይታው በሥራውና በጠባዩ መሻሻል ማሳየትና ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ አለመሆን ናቸው፡፡[92] እነዚህ መስፈርቶች ከተሟሉና ታራሚው ቢለቀቅ ከማህበረሰቡ ጋር በመልካም ሁኔታ ሊኖር የሚያስችለው መልካም ጠባይ አለው ተብሎ ከታመነበት በአመክሮ ሊለቀቅ ይችላል፡፡ ሆኖም በአመክሮ መለቀቅ ሙሉ በሙሉ ነጻነትን የሚያጎናጽፍ ሳይሆን ይልቁንም የቀረውን 1/3ኛ ቅጣት ታራሚው በገደብ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል ክትትል ሥር ሆኖ እንዲፈጽም የሚደረግበት የቅጣት አፈጻጸም ሥርዓት ነው፡፡[93] የዚህን ቅጣት አፈጻጸም ሥርዓት የበለጠ ፍሬያማ ለማድረግ የአመክሮ ተጠቃሚው በተጨማሪ የፈተና ጊዜ እንዲቆይ የሚደረግበትን አሰራር ለማበጀት ለፍርድ ቤቶች የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ሥልጣን ሰጥቷል፡፡[94] በዚህ ድንጋጌ መሠረት አመክሮን የሚወስነው ፍርድ ቤት የአመክሮ ተጠቃሚው በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ለመወሰን አንዳንድ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይወስናል፡፡ የፈተና ጊዜውም በማንኛውም ሁኔታ ከሁለት ዓመት ሊያንስ ከአምስት ዓመት ሊበልጥ እንደማይችል ሕጉ ይደነግጋል፡፡[95] ሆኖም በአመክሮ የሚለቀቀው ሰው የእድሜ ልክ እስረኛ በሆነ ጊዜ ፈተናው ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት እንዲሆን በልዩ ሁኔታ ሊወሰን ይችላል፡፡[96] እንዲህ አይነቱ ልዩ ውሳኔ በፍርድ ቤት በአመክሮ ጊዜ ካልተሰጠ የፈተና ጊዜው በፍርድ የተመለከተው የቅጣት ዘመን ሲጠናቀቅ የፈተና ጊዜው አብሮ እንደተጠናቀቀ የሕግ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡[97]

በአመክሮ የሚለቀቀው ሰው በፈተና ጊዜ ሊከተላቸው የሚገባ የጸባይ አመራር ደንቦች በሕጉ በግልጽ ተደንግገዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ ደንቦች በአመክሮ ተጠቃሚው ተግባራዊ ይደረጉ ዘንድ

---

[90] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 201

[91] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 202

[92] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 2002

[93] ዝኒ ከማሁን ሕግ፣ አንቀጽ 201 እና 204 ይመለከቷል

[94] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 204

[95] ዝኒ ከማሁ

[96] ዝኒ ከማሁ

[97] ዝኒ ከማሁ

ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ፍርድ ውስጥ በግልጽ መታዘዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የአመክሮ ተጠቃሚውም እነዚህን የጸባይ ደንቦች በሙከራ ጊዜው ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡፡[98] በፍርዱ መሠረት የጸባይ አመራር ደንቦችን ግለሰቡ የማክበር ግዴታ ሲኖርበት እንደ አስፈላጊነቱ አፈጻጸሙን የሚከታተል ባለሙያ ተመድቦ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ ሕጉ ጨምሮ ያዝዛል፡፡[99] ገደብና ቁጥጥሩን ተላልፎ ወይም ሌላ ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ወደ ነበረበት ማረሚያ ቤት ከመመለሱም በላይ ቀሪው ቅጣት አዲስ ለፈጸመው ወንጀል በፍርድ ቤት ከተጣለበት ቅጣት ጋር ተደምሮ ለመፈጸም እንደሚገደድ ሕጉ በአጽንኦት ይደነግጋል፡፡[100] በሕጉ ከተመለከቱት የአመክሮ ቅድመሁኔታዎች መካከል አንዱና መሠረታዊ የሆነው የባሕርይ መሻሻል እንዴት ይለካል? የሚለው ሐሳብ በሕጉ በደምሳሳው የታለፈ ነው፡፡ በመሆኑም ከወንጀል ሕጉ በተጨማሪ አመክሮን ለማስፈጸም ወጥተው ሥራ ላይ እየዋሉ ያሉ ዝርዝር መመሪያዎችን መመልከቱ ከፍ ብሎ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ ፋይዳው ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት በተደረገበት ማረሚያ ቤት እየተሰራበት ያለውን በአብክመ አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ቢሮ የወጣውን መመሪያ ለዚህ ጥናት ዓላማ መመልከቱ ተገቢነት ያለው ጉዳይ ይሆናል፡፡

---

[98] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 205 እና አንቀጽ 198. በእነዚህ አናቅጽ ሥር የደነገጉትን የጸባይ ደንቦች እንሆ!

**የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 205፡- የጠባይ አመራርና ቁጥጥር ደንብ**

1. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት የተለቀቀው ጥፋተኛ ለፈተና በተወሰነለት ጊዜ ተገቢ የሆነውን የጠባይ አመራር ደንብ/አንቀጽ 198 እንዲከተል ይወሰንበታል፤

   የተለቀቀው ጥፋተኛ ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦች የሚወሰኑት በተለይ የተለቃቂውን እድሜና ጠባዩን፣ ከተፈታ በኋላ ሊደርስበት የሚችለውን ለወንጀል የመጋለጥ እድል፣ የቤተሰቡን አስተማማኝነት፣ የሙያ ስራና የማህበራዊ ኑሮውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ነው፤

   የሚቻልም ሲሆን ለተለቃቂው መተዳደሪያ የሚሆኑት ሁኔታዎች ተቀጪው ከመለቀቁ በፊት በሚመለከተው ተቋም ወይም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ስልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ባልደረቦች ወይም አግባብ ባለው መንግስታዊ አካል ድጋፍ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

2. በመሰረቱ በሌላ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር ተለቃቂው በአንድ አሳዳሪ ወይም በአንድ የጠባቂነት ስልጣን በተሰጠው ባልደረባ ተቆጣጣሪነትና መሪነት ስር እንዲቆይ/ አንጽ 208፡፡ ይህም የጥንቃቄ ስርአት ሊፈጸም የማይቻልበት ሁኔታ ካጋጠመና ጠቃሚነት የሌለው መሆኑ ከታወቀ በተለቃቂው ላይ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል፡፡

   በዚህም መሠረት በአመክሮ የሚለቀቀው ጥፋተኛ በፈተናው ጊዜ ሊከተላቸው የሚገቡ የጠባይ አመራር ደንቦች በአንቀጽ 198 የተመለከቱ ሲሆን ድንጋጌውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**አንቀጽ 198 በጥፋተኛው ላይ የሚወሰን የጠባይ አመራር ደንብ**

1. ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስለው የታዩትን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የቁጥጥር ደንቦች በፍርዱ ላይ ይወስናል፡፡

   እነዚህ ደንቦች በተለይ በአንድ የጥበብ መስክ ሙያ መማርን፣ በተወሰነ ስፍራ የመቀመጥን፣ የመስራትን ወይም የመኖርን ግዴታ፣ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር እንዳይገናኝ መከልከልን ወይም በአንዳንድ በተወሰኑ ስፍራዎች ከመድረስ መታገድን፣ አልኮል መጠጣት የመከልከልን፣ በስራ ከሚያገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለቤተሰቡ፣ ለለሞግዚቱ ወይም ለአሳዳሪው መስጠትን፣ አስፈላጊ የሆነውን ህክምና መፈጸምን ወይም የሙከራውን ጊዜ ውጤት ፍሬ ለማስገኘት የሚችል ለዚሁ ተገቢ የሆነውንና ይህን የመሳሰለውን ሌላ የአመራር ደንብ የመፈጸም ግዴታን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2. በጥፋተኛው ላይ የሚወሰኑት የጠባይ አመራር ደንቦች የጥፋተኛውን አቅምና ፍላጎት፣ የነገሩን ሁኔታና ጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የጥፋተኛውን ጠባይ በማሻሻል ወደታሰበው ግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡

   የጠባይ አመራር ደንቡ ግብ ከፍርድ ማገድ ግብ ልዩ ሊሆንና ከሕጉም ጋር የማይስማሙ ግዴታዎችን ሊያስከትል አይችልም፡፡

3. አዲስ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርዱ በታገደለት ሰው፣ በባልደረባቸው፣ በሞግዚቱ ወይም በዋሱ አመልካችነት ወይም በዓቃቤ ሕግ ጠያቂነት የተወሰኑት የጠባይ አመራር ደንቦች ሊለወጡ ይችላሉ፡፡

[99] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 205(2)

[100] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 206 እና 207

### 5.2 አመክሮ በአማራ ብሔራዊ ክልል የሕግ ማዕቀፍ

በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግንና ሌሎች የክልሉ መንግሥት ሕጎችን መሠረት በማድረግ አመክሮ ለታራሚዎች ይሰጣል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር ሁኔታዎችን የያዙ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ መንግሥት ወጥተው ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም የሕግ ታራሚዎች አያያዝና አጠባበቅ መወሰኛ ደንብና የአመክሮ አሰጣጥ ሥርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣ ጊዜያዊ መመሪያ ናቸው፡፡ ደንቡና መመሪያው አመክሮን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከወንጀል ሕጉ በተጨማሪ በክልሉ እየተሰራባቸው ይገኛሉ፡፡ በወንጀል ሕጉ የተመለከቱት የአመክሮ መሠረታዊ መርሆዎች በቀደመው የጥናቱ ክፍል የቀረቡ በመሆኑ በዚህ ክፍል የክልሉ ደንብና መመሪያ የያዟቸውን አመክሮን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

በወንጀል ሕጉ የተመለከተውን አመክሮ በክልሉ በተሟላ መልኩ ለመፈጸም የሚያግዝ ደንብ በ1997 ወጥቶ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ ደንቡም ታራሚዎችን በአመክሮ ለመልቀቅ የሚያስችል አሠራርና መስፈርት አለው፡፡ በደንቡ የተካተቱ የአመክሮ ቅድመ-ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 ሥር ከተመለከቱት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው፡፡[101] ሆኖም ደንቡ በወንጀል ሕግ በግልጽ ከተመለከቱት ቅድመሁኔታዎች በተጨማሪ እድሜያቸው ከ70 ዓመት በላይ የሆነ አዛውንቶች፣ የአእምሮ ሕመም ያለባቸውና ሌሎች በማይድን በሽታ እየተሰቃዩ ያሉ ታራሚዎች፣ ይኸው በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ የአመክሮ ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ልዩ ሁኔታን ደንግጓል፡፡[102] የቅድመሁኔታዎችን መሟላት እያረጋገጠ የአመክሮ ተጠቃሚዎችን ለይቶ በማቅረብ ረገድ ኃላፊነትን የሚሸከም ኮሚቴ በክልሉ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ መቋቋም እንዳለበት ይኸው ደንብ ደንግጓል፡፡[103] በመሆኑም ኮሚቴው በወንጀል ሕጉና በደንቡ የተመለከቱትን ቅድመሁኔታዎች በአመክሮ የሚለቀቀው ታራሚ ያቀረበውን ማመልከቻና ማስረጃ በመመርመር የውሳኔ ሐሳብ የማቅረብ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡[104]

ከአመክሮ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና አፈጻጸም አኳያ ሊፈተሽ የሚገባው ሌላው ሕግ የአብክመ የአመክሮ አሠጣጥ ሥርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣው ጊዜያዊ መመሪያ ቁጥር 1/2003 ዓ.ም ነው፡፡ መመሪያው በወንጀል ሕጉና በአብክመ የሕግ ታራሚዎች አያያዝና አጠባበቅ ደንብ የተመለከቱትን የአመክሮ ቅድመሁኔታዎች በዝርዝር ለመወሰንና ለማስፈጸም የወጣ ነው፡፡ በተጨማሪም በፍርድ ቤቶች ሲሰጥ የነበረው አመክሮ በማረሚያ ቤቶች በኩል እንዲፈጸም በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የተደረሰውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አሠራርን ለመዘርጋት ታስቦ የወጣ መመሪያ ነው፡፡[105] መመሪያው በወንጀል ሕጉና በደንቡ የተመለከቱትን የአመክሮ ቅድመሁኔታዎችና መሥፈርቶች ይበልጥ ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ በማስፈር በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች እንዲሁም ታራሚዎች በቀላሉ እንዲረዷቸውና እንዲጠቀሙባቸው አድርጓል፡፡ በዚህ

---

[101] የሕግ ታራሚዎች አያያዝ እና አጠባበቅ ለመወሰን የወጣ ደንብ፣ ደንብ ቁጥር 26/97፣ ዝክረ-ሕግ፣ 1997፣ ቁጥር 49፣ አንቀጽ 48/2

[102] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 48 (1) (መ)

[103] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 47

[104] ዝኒ ከማሁ

[105] የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 15፣ የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ግኝትን መሠረት በማድረግ በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አመክሮ በማረሚያ ቤቶች ውሳኔ መሠረት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለተጨማሪ ማብራሪያ የመመሪያውን መግቢያ ይመለከቷል፤

መሠረት አመክሮ የሚያሰጡ፣ የሚያዘገዩና የሚያሳግዱ ወይም የሚያስከለክሉ ሁኔታዎችን በዝርዝር ያመለከተ ሲሆን፣ በአመክሮ አሰጣጥ ስነሥርዓትና አጠቃላይ አፈጻጸም ውስጥ ትልቅ ሚናን በመጫወት ላይ ይገኛል። አመክሮን ለመስጠት መሟላት ያለባቸው በወንጀል ሕጉና በደንቡ የተመለከቱ ቅድመሁኔታዎች በመመሪያውም የተመለከቱ ሲሆን[106]፣ ከእነዚህ ቅድመሁኔታዎች መካከል አንዱ የሆነውን የታራሚው ባሕርይ መሻሻልን ለመመዘን የሚያስችሉ ከ100 የሚታሰቡ ነጥቦችን[107] በዝርዝር በማመልከት የወንጀል ሕጉንና ደንቡን ለማስፈጸም የሚያግዝ ሥርዓትን ዘርግቷል። መመሪያው ታራሚው የጸባይ ለውጥ ማምጣቱን ለመመዘን ከ100 ውጤት እንዲሰጠው ያመላከተ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት ከ75 በላይ ውጤት ያስመዘገበ እንደሆነ ለአመክሮ ብቁ ይሆናል። የእነዚህ ቅድመሁኔታዎችና የሌሎች በመመሪያው የተመለከቱ ተያያዥ መሥፈርቶች አለመሟላት ለምሳሌ፣ ታራሚው ከእሥራት ቅጣት በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ተወስኖበት ከሆነ መቀጮውን አለመክፈሉ አመክሮን እንደሚያዘገይ ወይም እንደሚያሳግድ መመሪያው በተጨማሪ ደንግጓል።[108] በአጠቃላይ በአማራ ክልል አመክሮን አስመልክቶ ያለው የሕግ ማእቀፍ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ከኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ጋር በተለይ መመሪያው ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነትና አልፎ አልፎም ተቃርኖ ስላለው በሚቀጥለው የዚህ ጥናት ክፍል ይህንኑ ለማሳየት ተሞክሯል።

## 5.3 በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግና በአብክመ አመክሮ አሰጣጥ መመሪያ መካከል የሚስተዋሉ ልዩነቶችና ለአፈጻጸም የሚያስቸግሩ መስፈርቶች

የወንጀል ሕጉ አመክሮንና ተያያዥ ጉዳዮችን ማለትም በአመክሮ ጊዜ የሚሰጥ የፈተና ጊዜ፣ ከእሥራት ቅጣት በተጨማሪ በፍርድ ቤቱ የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲሁም ሌሎች መሰል ጉዳዮችን የመወሰን ሥልጣንን ለፍርድ ቤቶች የሰጠ ሲሆን[109]፣ መመሪያው ደግሞ በሁለቱ ተቋማት ስምምነት መሠረት አመክሮ ታራሚዎቹ በየሚገኙበት ማረሚያ ቤቶች እንዲሰጥ አድርጓል።[110] ይህም የሆነው በክልሉ በተደረገ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው የአመክሮ አሰራር በታራሚዎች ላይ እንግልትን የሚፈጥርና የተንዛዛ የሥራ አካሄድ ያለበት እንደሆነ በመታመኑና አመክሮን የመስጠት ሥልጣን በመመሪያው ለማረሚያ ቤቶች መሰጠቱ ነው።[111] ይሁን እንጂ አመክሮን የመወሰን ስልጣን ለማረሚያ ቤቶች መሰጠቱ በወንጀል ሕጉ ለፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የተሰጣቸውን ሥልጣን ይጋፋል። በተጨማሪም መመሪያው በወንጀል ከአመክሮ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ለምሳሌ፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 204 ሥር የተመለከተውን የፈተና ጊዜ በማን እንደሚፈጸሙ መመሪያው ባለማመልከቱ የሕግና የአሰራር ክፍተትን ፈጥሯል። ይህ መመሪያ ከወንጀል ሕጉ ጋር መቃረኑና እየተሰራበት ያለ መሆኑ ከአጠቃላይ የሕግ መርህ አንጻር ሲታይ ትክክል ነውን? የሚለው ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ትኩረትና ምላሽ የሚሻ ስለመሆኑ አመላካች ነው።

ሌላው በመመሪያውና በወንጀል ሕጉ መካከል የሚታየው የሐሳብ ልዩነት ከአመክሮ መስፈርቶች ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ረገድ ሊታይ የሚገባው የአመክሮ መስፈርት

---

[106] የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ፣ ግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 15፣ ቁጥር 4.2 (1-5)

[107] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 4.3 (1-9)

[108] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6ን ይመልከቱ

[109] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 202፣ 204-207

[110] የሕግ ታራሚዎች አያያዝና አጠባበቅ ለመወሰን የወጣ ደንብ፣ግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 101፣ አንቀጽ 46

[111] የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሪፖርት፣ ግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 17፣ ገጽ 54ና 55

"ልማደኛ ደጋጋሚ አለመሆን" የሚለው ነው፡፡[112] በልማደኛ ደጋጋሚነትና በደጋጋሚ ወንጀለኛ (recidivist)[113] በሚሉት ጽንሰ ሐሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ ተገንዝቦ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ግልጽ ያለመሆን ችግር ይስተዋላል፡፡[114] ስለ አመክሮ በሚደነግገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 ሥር የተመለከተውን አመክሮን ከሚያስከለክሉ ሁኔታዎች ውስጥ ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆን ሲሆን፣ የዚህ ድንጋጌ ጽንሰ-ሐሳብ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 67 ሥር ከተመለከተው ደጋጋሚ ወንጀለኛ የተለየ እንደሆነ የሕጉን ሐተታ ዘምክንያት በመመልከት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ልማደኛ ደጋጋሚ ማለት ወንጀለኞች በተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊትን ሲፈጽሙ እንደሆነ ከዚሁ ትንታኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ደጋጋሚነት ግን ወንጀለኛው ከዚህ በፊት ጥፋተኛ ተብሎ የእሥራት ጊዜውን ጨርሶ ወይም በሕግ እንዲፈታ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ባሉት አምስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ሌላ ወንጀል ሆነ ብሎ ከፈጸመና ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሲታይ ዝቅትኛው የአሥራት መጠን ስድስት ወርና ከዚያ በላይ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ ከሆነ ነው፡፡[115] ከዚህ ትርጓሜ መረዳት እንደሚቻለው ደጋጋሚነትና ልማደኛ ደጋጋሚነት ሁለት የተለያዩ ጽንሰሐሳቦችና በውጤት ደረጃም የተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ ሐተታ ዘምክንያት ይህንን ልዩነት ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ በመስጠት ለማብራራት ሞክሯል፡፡

> …ለምሳሌ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ተራ ሥርቆት (አንቀጽ 665) እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት ቢያስቀጣም መነሻ ቅጣቱ 10 ቀን ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተራ ሌባ ደጋጋሚ ነው ላይባል ነው፤ ደጋጋሚ ነው ካልተባለም ልማደኛ ሌባ ነው የሚባልበት ጊዜ አይኖርም፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ሌባ ቀን በቀን ከሜዳ ላይ በሬ በመስረቁ የተፈረደበትን የቀላል ወይም የጽኑ እሥራት ቅጣት ከጨረሰ በኋላ አምስት ዓመት ሳይሞላው ከታክሲ ተሳፋሪ ላይ ዘጠኝ መቶ ብር ቢሰርቅ ደጋጋሚ ሌባ ሊባል አይችልም፤ ምክንያቱም የተራ ሥርቆት መነሻ ቅጣት 10 ቀን እንጂ 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ ባለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልክ አምስት ወይም ከአምስት የሚበልጥ የሥርቆት ሪከርድ ያለበት ሌባ ልማደኛ ሌባ ሊባል አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ አተረጓጎም ግን የኢትዮጵያን ህዝብና ሕግ አውጭውን ሐሳብ ይጻረራል፤ የሁለቱም ዓላማ የተጠቀሰው አይነቱ ሌባ ልማደኛ ወይም ደጋጋሚ ተብሎ ከባድ ቅጣት እነዲወሰንበት ነው፡፡ …..በደጋጋሚነት በሥርቆት ብዙ ጊዜ ከተቀጣም ልማደኛ ሌባ ነው ተብሎ ከባድ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡፡ ልማደኛ ሌባ ከሆነም የተፈረደበትን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ከመጨርስ በቀር በአመክሮ የመፈታት እድል አይኖረውም፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ህዝብና ከሕግ አውጭው ዓላማ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡"[116]

ከዚህ ትርጓሜ መረዳት የሚቻለው በደጋጋሚ ወንጀለኛና በልማደኛ ደጋጋሚነት መካከል የጽንሰ-ሐሳብና የሕጋዊ ውጤት ልዩነት እንዳለና በሕግ አውጭው ሐሳብ ልማደኛ ደጋጋሚነት አመክሮን የሚያስከለክል፤ አደገኛነትን የሚያሳይ የወንጀለኞች ባሕርይ ሲሆን፣ ደጋጋሚነት ግን ቅጣትን ለማክበድ እንጂ አመክሮን የሚያስከለክል ጉዳይ እንዳልሆነ ነው፡፡ የሁለቱን ጽንሰሐሳቦች ልዩነት ይበልጥ ለመገንዘብ የወንጀል ሕጉ ደጋጋሚና ልማደኛ ድጋጋሚነት በቅጣት አወሳሰን ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ያመለከቱበትን አግባብ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ደጋጋሚነት በልዩ የቅጣት ማክበጃነት በቀረበ ጊዜ ጉዳዩን በዳኝነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ የሚወስነውን የእሥራት ቅጣት

---

112 የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 202(2)

113 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 67

114 በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት፣ ከማረሚያ ቤቱ ባለሙያዎች፣ የሥራ ሃላፊዎችና ታራሚዎች ጋር በአመክሮ አሰጣጥ ላይ የተደረገ የቡድን ወይይት፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም

115 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ አንቀጽ 67

116 ዝኒ ከማሁ

ወንጀለኛው ጥፋተኛ ከተባለበት በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በማለፍ ሊወስን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በፍርድ ቤቱ የሚወሰነውን ቅጣት የተፈጸመው አዲስ ወንጀል ወይም ተደራራቢ ወንጀል ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል የተመለከተውን ቅጣት እስከ እጥፍ ሊደርስ የሚችል ቅጣት ሊወስን ይችላል፤ የተፈጸመውን የወንጀል አይነት ክብደትና ብዛት እንዲሁም የወንጀለኛውን ባሕርይ አደገኛነት ግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከተውን የእሥራት ጣሪያ ሊደርስ የሚችል ቅጣት ሊወስንበት እንደሚችል ድንጋጌው በተጨማሪ አመልክቷል፡፡[117] ይኸው ድንጋጌ ደጋጋሚ የሚለውን ጽንሰሐሳብ ከልማደኛ ደጋጋሚ በመለየት ለልማደኛ ደጋጋሚ ከፍ ብሎ ከተመለከተው የቅጣት አወሳሰን የተለየ ድንጋጌን አመልክቷል፡፡ ድንጋጌው ጥፋተኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከተውን ቅጣት እጥፍ በማለፍ ቅጣት የመወሰኑ ጉዳይ የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ሥልጣን መሆኑ ቀርቶ አስገዳጅ እንደሆነ አመልክቷል፡፡[118] ይህም ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከደጋጋሚው ይልቅ አደገኛ ባሕርይ ያለውና ሊጣልበት የሚገባው ቅጣት ከፍተኛ የመሆኑ ጉዳይ ከፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ይልቅ በሕግ አውጭው የተወሰነና ግዴታ መፈጸም ያለበት መሆኑን በማመላከት በሁለቱ ጽንሰ-ሐሳቦች መካከል ያለው ልዩነት በሕግ አውጭው ተገቢውን እይታ ያገኘ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንን ይበልጥ የሚያጠክረው ሌላው አንኳር ነጥብ ስለአመክሮ የሚገልጸው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 በግልጽ አመክሮን የሚያስከለክለው ልማደኛ ደጋጋሚነት (persistent recidivist) መሆኑን ያመላከተ በመሆኑና በዚሁ ሕግ አንቀጽ 67 ሥር የተደነገገው ስለደጋጋሚነት (recidivisim) በመሆኑ በሕግ አደረጃጀት ረገድ ተመሳሳይ ሐሳብን በተለያየ አገላለጽ መጠቀም የሕጉን ግልጽነት ስለሚያጠፋው ሁለቱ ሐሳቦች የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በወንጀል ሕጉ አመክሮን ሙሉ በሙሉ የሚያስከለክለው ልማደኛ ደጋጋሚነት እንጂ ደጋጋሚነት አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአብክመ የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ በቁጥር 4(2) ሥር አመክሮን ከሚያስከለክሉ ሁኔታዎች መካከል ከዚህ በፊት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለና ሪኮርድ ያለበት ከሆነ አመክሮ እንደማይሰጠው ያመላክታል፡፡ በዚህ ረገድ መመሪያው ከላይ ከተገለጸውና ከተብራራው የወንጀል ሕጉ መንፈስ ጋር የሚቃረንና አመክሮን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎችን አስፍቶ በመተርጎም የአመክሮን መሠረታዊ አስፈላጊነት በሚያጣብብ መንገድ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አተረጓጎም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 67 እንዲሁም 202 ሥር የተመለከቱትን ሐሳቦች እንዲሁም ከነዚህ ውጭ የሆነን ያለፈ የወንጀል ሪኮርድ ያለበትን ሰው ሙሉ በሙሉ ከአመክሮ የሚከለክል ይመስላል፡፡ በመሆኑም ደጋጋሚና ልማደኛ ደጋጋሚ ተብለው በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 እና 202 እንደ ቅደምተከተላቸው የተደነገጉት ከመመሪያው ጋር ተገናዝበው ሊተረጎሙ ስለሚገባ መመሪያው የወንጀል ሕጉን ጽነሰሐሳብ በማይቃረን መልኩ ሊከለስ ወይም ሊሻሻል ይገባዋል፡፡

ይህንን ጽንሰ-ሐሳብ በተመለከተ ያለውን ብዥታ ለማጥናት በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት በተደረገ ውይይት ይኸው ችግር ተስተውሏል፡፡[119] ተወያዮች በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 እና 202 መሠረት ደጋጋሚ መሆኑ የተረጋገጠ ታራሚ የአመክሮ ተጠቃሚ እንደማይሆን ቢታወቅም ጽንሰ-ሐሳቡን በመረዳትና በመተግበር ረገድ ብዥታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ የወንጀል መረጃን አጠናቅሮ በአንድ ቋት ሊይዝ የሚችል ራሱን የቻለ አካል በሀገር አቀፍም ይሁን በክልል ደረጃ ተለይቶ አለመቋቋሙ ለማረሚያ ቤትም ይሁን ለፍርድ

---

[117] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 188 (1 እና 2)

[118] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 188 (2 -ሁለተኛው አንጓ)

[119] በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት፣ ከማረሚያ ቤቱ ባለሙያዎች፣ የስራ ሃላፊዎችና ታራሚዎች ጋር በአመክሮ አሰጣጥ ላይ የተደረገ የቡድን ወይይት፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም.

ቤት ደጋጋሚና ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኞችን በሕጉ መንፈስ ለመቅጣትና ለማረም አስቸጋሪ እንደሆነ በውይይቱ ተሳታፊዎች ሐሳቡ ተወስቷል፡፡ በአብክመ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማረምና ማነጽ የሥራ ሂደት ኃላፊ ጋር በተደረገ ውይይትም ይኸው ችግር እንዳለ ተገልጾ ደጋጋሚነና ልማደኛ ደጋጋሚነትን ባልየ መልኩ የደጋጋሚ ወንጀለኞች ቁጥር እየጨመረ መሆኑን የሚያሳይ አህዛዊ መረጃ በአመታዊ የሥራ ሪፖረት ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት የ2009 ዓ.ም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት 1238 የሚደርሱ ታራሚዎች ደጋጋሚ ወንጀለኞች እንደሆኑና ይህም በክልሉ ያሉ ታራሚዎችን 5.5 በመቶ የሚሆን ቁጥር እንደሚሸፍን ያመለክታል፡፡[120] ይህ ደጋጋሚነትና ልማደኛ ደጋጋሚነት በተግባር ያለ መሆኑን ያሳይ እንጂ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ ተገቢውን ግንዛቤ አግኝቶ በተግባር ተለይቶ መረጃ እንደማይያዝ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ደጋጋሚና ልማደኛ ደጋጋሚ በባሕር ዳር ማረሚያ ቤትም ይሁን በአጠቃላይ የወንጀል ፍትህ ሥርዓት አይነተኛ ችግር መሆኑን ተገንዝቦ ያለውን የጽንሰሐሳብ ብዥታና የአፈጻጸም ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ሌላው በወንጀል ሕጉና በመመሪያው መካከል ልዩነት እንዳለ የሚያሳየው የአመክሮ መስፈርት እርቅ ነው፡፡ እርቅ በአመክሮ የሚለቀቀው ሰው የወንጀሉ ሰለባ ከሆኑ ግለሰቦችና ዘመዶቻቸው ጋር መልካም ግንኙነትን እንዲፈጥርና በበቀል ተነሳስቶ ተጨማሪ ወንጀሎች በመካከላቸው እንዳይፈጸሙ በማድረግ በኩል የላቀ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 (1) (ለ) ታራሚው በፍርድ ወይም በስምምነት የተወሰነበትን ካሳ ለተበዳዩ የመክፈል ግዴታን እንደ ቅድመሁኔታ በግልጽ ሲያመላክት በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊፈጸም የሚገባውን እርቅ አልፎታል፡፡ በመመሪያው ቁጥር 4.3 (4) ላይ እንደተመለከተው የተፈጸመው ወንጀል በግለሰብ ላይ በደልን ወይም ጉዳትን የሚያደርስ በተለይም የሰው መግደል ወንጀል፣ የመግደል ሙከራና አስገድዶ መድፈር በሆነ ጊዜ ከግል ተበዳዮች ጋር እርቅ መፈጸም ለአመክሮ የሚያስፈልግ መስፈርት ወይም ቅድመሁኔታ ሆኖ ተመልክቷል፡፡ ይህን በወንጀል ሕጉ ያልተመለከተ የአመክሮ ቅድመሁኔታ መመሪያው መጠየቁ በሁለቱ መካከል መጣረስን ያስከተለ ይመስላል፡፡

ይህ ቢሆንም መመሪያው እርቅን በቅድመሁኔታነት ማኖሩ በአመክሮ ተጠቃሚዎችና በግል ተበዳዮች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ እንዳለው ግልጽ ነው፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት መመሪያው እርቅን የአመክሮ አንድ መስፈርት አድርጎ ያመላከተ ቢሆንም በወንጀል ሕጉ ካለመመልከቱም በላይ በተግባር ከእርቅ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ለዚህ ጥናት ዋቢ በመሆን ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ታራሚዎችና ባለሙያዎች አውስተዋል፡፡[121] ምንም እንኳ በአመክሮ የሚለቀቁ ታራሚዎች ከተጎጂው ወይም ከቤተሰቦቹ ጋር እርቅ እንዲፈጽሙ መደረጉ በመሰረተሐሳብ ደረጃ መልካም ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ማረሚያ ቤት የቆዩ ሰዎች ከባላንጋራዎቻቸው ጋር እርቅ እንዲፈጽሙ ሲገደዱ በአፈጻጸም ስለሚቸገሩ አመክሮን አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህን ግምት ውስጥ ያስገባ በሚመስል መልኩ እርቅ መፈጸም ከአመክሮ መስፈርቶች አንዱ ሆኖ በመመሪያው ቢካተትም የተሰጠው ዋጋ ዝቅተኛ[122] ከመሆኑም በላይ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም፡፡[123]

---

[120] ኮማንደር አማረ ወርቁ፣ በአብክመ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ማረምና ማነጽ የስራ ሂደት ባለቤት፣ በአመክሮ ላይ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ሐማሌ 2009 ዓ.ም.

[121] ኮማንደር እውነቱ፣ በአብክመ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የማረምና ማነጽ ባለሙያ፣ ስለአመክሮ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ባሕር ዳር፣ግንቦት 2008

[122] የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ፣ የግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 15 እንደተገለጸው፣ ቁጥር 4.3 (4)

[123] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 188 (2 ሁለተኛው አንቀ)

ታራሚው የአመክሮ ተጠቃሚ ለመሆን የባሕርይውን መሻሻል ሊያሳዩ የሚችሉ መስፈርቶችን ከማሟላቱ በተጨማሪ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ከተበዳዮች ጋር በተደረገ ሥምምነት መሠረት ለደረሰው ጉዳት ካሳ መክፈል ለአመክሮ እንደአንድ ቅድመሁኔታ ሆኖ እንደሚያገለግል የወንጀል ሕጉ[124] እና መመሪያው[125] ያመላክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በተግባር የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ ከባለሙያዎችና ከሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት ተረጋግጧል፡፡[126]

ሌላው ከአመክሮ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር አመክሮን የሚያስከለክሉ ወይም የሚያዘገዩ ተብለው በመመሪያው የተዘረዘሩ ወንጀሎች ጉዳይ ነው፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 11 (ሰ) ሥር አመክሮን የሚያስከለክሉ ወይም የሚያዘገዩ ተብለው የተገለጹ ወንጀሎች ሲታዩ በባሕርያቸው ከባድና በህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን የሚያስከትሉ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ሆን ብሎ ሰው በመግደል፣ በዘረፋ፣ በአስገድዶ መድፈር፣ በሕገ-መንግሥቱና በመንግሥት ላይ አድማ መጠንሰስና በመሰል ከባድ ወንጀሎች መጠርጠር ወይም መከሰስ አመክሮን ለማስከልከል ወይም ለማዘግየት በቂ ምክንያት እንደሆኑ ተመልክተዋል፡፡[127] ሆኖም ይህ አይነቱ ክልከላ ከሕግ አንጻር ሲታይ ተቀባይነቱ አነጋጋሪ ነው፡፡ በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩት አመክሮን ሊያዘገዩ ወይም ሊያስከለክሉ የሚችሉ የወንጀል አይነቶች በወንጀል ሕጉ አመክሮን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች በገደብነት ያልተመለከቱ ከመሆናቸውም በላይ ታራሚው በእነዚህ ወንጀሎች በመጠርጠሩ ብቻ የአመክሮ ተጠቃሚ እንዳይሆን መከልከሉ የተጠረጠረባቸውን ወንጀሎች በተመለከተ እንደንጹህ የመገመት መብቱ ላይ ተጽእኖ ያሳርፋል፡፡

አመክሮን ሊያሳግድ ወይም ሊያዘገይ የሚችል በመመሪያው የተመለከተ ሌላው ነገር ታራሚው ከእሥራት ቅጣቱ በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ተወስኖበት ከሆነ ይህንን አለመፈጸሙ ነው፡፡[128] የገንዘብ መቀጮ ያለበት ታራሚ በወንጀል ሕጉ የተመለከቱትን የአመክሮ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ቢገኝም መቀጮውን እስካልከፈለ ድረስ በአመክሮ የመለቀቅ እድል አይኖረውም፡፡ ይህም በወንጀል ሕጉ ያልተካተተና ከእሥራት ቅጣቱ ጋር ግንኙነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ታራሚው መቀጮውን እንዲፈጽም ለማድረግ ሌላ ሥልጣን ያለው አካል ሌሎች ስልቶችን[129] ተጠቅሞ በማስፈፀም ፋንታ የአመክሮ ተጠቃሚ እንዳይሆን ታራሚውን መከልከሉ የሕግ መሠረት የሌለው አሠራር ነው፡፡

በወንጀል ሕጉና በመመሪያው ከተመለከቱት የአመክሮ መስፈርቶች መካከል አንዱ በፍርድ ቤቱ ከተወሰነው የእሥራት ቅጣት ውስጥ 2/3ኛውን መፈጸም፤ የሚለው ነው፡፡ ይህንን ነጥብ በተመለከተ ሕጉና መመሪያው ልዩነት የማይታይባቸው ቢሆንም የመስፈርቱን

---

[124] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 1 ላይ እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 202 (1) (ለ))

[125] የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ፣ የግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 15 እንደተገለጸው፣ ቁጥር 4.2 (2)

[126] ኮማንደር አማረ ወርቁ፣በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 120 እንደተገለጸው

[127] የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ፣ የግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 15 እንደተገለጸው፣ ቁጥር 11(ሰ)

[128] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 6.2 (3)

[129] የመቀጮ ቅጣት አወሳሰንና አፈጻጸምን በተመለከተ የተደነገጉትን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 90-96 ይመለከቷል፡፡ መቀጮ የተወሰነበት ታራሚ ገንዘቡን ወዲያውኑ መክፈል እንዳለበት በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 93 ስር የተመለከተ ሲሆን ይህን ማድረግ እንደማይችል ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ እንደሁኔታው ከአንድ እስከስድስት ወር ሊያራዝምለት እንደሚችል በዚሁ ድንጋጌ ተመልክቷል፤ እንደነገሩ ሁኔታም ክፍያው በጊዜ ተከፋፈሎ (by installment) ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ታራሚው እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ እነዚህን አማራጮች በመጠቀም ታራሚው መቀጮውን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ መቀጮው ወደጉልበት ስራ ተቀይሮ መፈጸም እንዳለበት በአንቀጽ 95 እና 96 ስር ተደንግጓል፡፡

ተግባራዊነት በተመለከተ በታራሚዎች በኩል የሚነሳ ችግር አለ፡፡ ይኸውም የእሥራት ቅጣቱ በፍርድ ቤት ሲወሰን ታራሚው ከፍርድ በፊት በፖሊስ ጣቢያ ወይም በማረፊያ ቤት የቆየበት የእሥራት ጊዜ በግልጽ በፍርድ መዝገቡ ላይ ባለመስፈሩ የ2/3ኛ የእሥራት ጊዜን ለማስላት የመረጃ ችግር ይፈጠራል፡፡ በሌላ አነጋገር ታራሚው ወንጀሉን እንደፈጸመ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የዋለበትን ጊዜ ለ2/3ኛ የእሥራት ጊዜ ስሌት መነሻ እንዲደረግለት ለፍርድ ቤቱ ባለማመልከቱ ሊታለፍ የሚችል ከመሆኑም በላይ በፍርድ መዝገቡ ይህ የሚገለጽበት አግባብ 'እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ' በሚል ፍርዱ ሲገለጽ በ2/3ኛ ጊዜ ስሌት ላይ ብዥታን ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም ታራሚው በፖሊስ በቁጥጥር ሥር የዋለበት ጊዜ በግልጽ አለመመልከቱ ወይም እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሚል በደምሳሳው መገለጹ ታራሚዎችን በሚያስተዳድረውና የእሥራት ጊዜውን በማስላት የአመክሮ ተጠቃሚዎችን ለሚለየው ማረሚያ ቤት ግልጽ የሆነ መረጃን ስለማይሰጥ ነው፡፡ ይህም ጥናቱ በተደረገበት ባሕር ዳር ማረሚያ ቤት በሚገኙ ታራሚዎች ላይ ከፍተኛ ቅሬታን የፈጠረና ለከፍተኛ ምሬትና እሮሮ የዳረገ መሆኑን በማረሚያ ቤቱ ከተደረገው ምልከታ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይ ታራሚዎች የአመክሮ ጊዜያቸውን በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋሉበት ጊዜ ጀምሮ በማስላት በአመክሮ መለቀቅ እንዳለባቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ በቁጥጥር ሥር ከነበሩበት ፖሊስ ጣቢያ ወይም ማረፊያ ቤት ማስረጃ እንዲያመጡ ሲጠየቁ ማስረጃውን የሚያመጣላቸው ሰው በማጣት መቸገራቸው ለቅሬታው ምክንያት እንደሆነ ታራሚዎች በአፅንኦት ያነሳሉ፡፡[130]

በአጠቃላይ አመክሮ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግና ሌሎች መመሪያዎች ላይ እውቅናን ያገኘና በስፋት እየተፈጸመ ያለ የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ አሰራር ቢሆንም በርካታ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች ያሉበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ በወንጀል ሕጉና በመመሪያው መካከል የሚንጸባረቁ ልዩነቶች እንዲሁም በወንጀል ሕጉና በመመሪያው በየራሳቸው ላይ የሚስተዋሉ የሕግ ክፍተቶች በአመክሮ ጽንሰሐሳብ ላይ ብዥታን የፈጠሩ በመሆናቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ለችግሩ ትኩረት በመስጠት በሕግ ማእቀፉ ላይ ማሻሻያ እንዲያደርጉ በዚህ ጥናት ተጠቁሟል፡፡

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳብ

በዚህ ጥናት አመክሮን በተመለከተ በርካታ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች የተለዩ ሲሆን፣ አንኳር አንኳር ችግሮችና የመፍትሄ ሐሳቦቻቸው እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል፤

አመክሮ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የታራሚዎችን የባሕርይ ለውጥ መሠረት አድርጎ የሚሰጥና ታራሚዎች ከእስር ተለቅቀው ወደ ማህበረሰቡ ተመልሰው ቀሪውን የቅጣት ጊዜ በሙከራ የሚያሳልፉበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ታራሚዎች ያሳዩትን የባሕርይ ለውጥ መሠረት በማድረግ የሚሰጠው አመክሮ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግና እሱን ለማስፈጸም በወጣ መመሪያ መሠረት ይመራል፡፡ ይህ ጥናት በተደረገበት ባሕር ዳር ማረሚያ ቤትም ከላይ የተጠቀሰው የወንጀል ሕግና በአብክመ የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ታራሚዎች በአመክሮ እንዲለቀቁ ይደረጋል፡፡ በጥናቱም በነዚህ የአመክሮ ሕጎችና አፈጻጸም ላይ የሚስተዋሉት ችግሮች ተለይተዋል፤ የመፍትሄ ሐሳብም ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሠረት በጥናቱ የተገኙ በርካታ የሕግ ክፍተቶች ያሉ ሲሆን፣ ክፍተቶቹ በአመክሮ አፈጻጸም ላይ ችግር አስከትለዋል፡፡ ከተለዩ የሕግ ክፍተቶች መካከል አንዱ የአብክመ

[130] አቶ ደሳለኝ ጥጋቡ፣ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት ነጻ የሕግ ድጋፍ መስጫ ማእከል ምክትል አስተባባሪ፣ አመክሮን በተመለከተ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ሐምሌ 27 ቀን 2009 ዓ.ም.

አመክሮ አሰጣጥ መመሪያ ከወንጀል ሕጉ ጋር ተጣጥሞ እንዲወጣ አለመደረጉ ነው፡፡ የአብክመ የአመክሮ አሠጣጥ ሥርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣ ጊዜያዊ መመሪያ ቁጥር 1/2003 አመክሮ በክልሉ ባሉ ማረሚያ ቤቶች አማካይነት እንዲሰጥ ማድረጉና ይኸም ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አሰራር የሀገሪቱ ሕግ አውጭ አካል ያወጣውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በግልጽ የሚጻረር ሆኖ ተግኝቷል፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሕግ አውጭው የተሰጠውን አመክሮን የመስጠት ሥልጣን በስምምነት ለማረሚያ ቤቶች መስጠቱ ከሕግ አኳያ ችግር ያለበት መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አመክሮን ከሚያስከለክሉ ሁኔታዎች መካከል ልማደኛ ደጋጋሚነትን አንዱ አድርጎ በአንቀጽ 202/2 ሥር ቢደነግግም ልማደኛ ደጋጋሚነት ምን እንደሆነ አለመግለጹ ሌላው የሕግ ክፍተት ነው፡፡ ይህን ተከትሎ የአመክሮ አሰጣጥ መመሪያው ደጋጋሚ ወንጀለኛነት አመክሮን እንደሚያስከለክል የገለጸ ቢሆንም የደጋጋሚ ወንጀለኛነትን ጽንሰሐሳብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 67 እና 202 ድንጋጌዎች መንፈስ ጋር በተጣጣመ መልኩ አላመላከተም፡፡ በመሆኑም ደጋጋሚና ልማደኛ ደጋጋሚ ከወንጀል ሕጉና ከአመክሮ አሰጣጥ መመሪያው አኳያ ሲታዩ እርስበርሳቸው የማይጣጣሙ በመሆናቸው በተግባር በአመክሮ አሰጣጥ ላይ የግልጽነት ችግር አለ፡፡

በሌላ በኩል የአመክሮ አፈጻጸም መመሪያው በወንጀል ሕጉ ያልተመለከተ አዲስ የአመክሮ ቅድመሁኔታ ይዟል፡፡ ይኸውም ታራሚዎች በወንጀል ድርጊታቸው ጉዳት ካደረሱባቸው ሰዎች ወይም ከተበዳይ ወገን ጋር እርቅ መፈጸም እንዳለባቸው መደንገጉ ነው፡፡ እርቅ በመርህ ደረጃ ጠቃሚና ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ከማህበረሰቡ ተለይተው በማረሚያ ቤት የቆዩት የአመክሮ ተጠቃሚዎች ከወንጀል ሰለባዎችና ቤተሰቦቻቸው ጋር ያለምንም ምቹ ሁኔታ እርቅ እንዲፈጽሙ መገደዳቸው በተግባር ጫና እያሳድረባቸው እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በመመሪያው ከተመለከቱት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል በከባድ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ታራሚዎች በነዚህ ወንጀሎች በመጠርጠራቸው ብቻ አመክሮው ሊዘገይ ወይም ሊታገድ እንደሚችል መገለጹ የተጠርጣሪዎችን እንደ ንጹህ ሰው የመገመት መብት ጥያቄ ውስጥ ያስገባል፡፡ በተጨማሪም ክልከላው በወንጀል ሕጉ ወይም በሌላ እናት ሕግ ያልተመለከተ በመሆኑ የመመሪያውን ሕጋዊነትና ተቀባይነት ከሕግ አወጣጥ መርህ አንጻር አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡ መመሪያው በወንጀል ሕጉ ባልተመለከተበት ሁኔታ ከእሥራቱ በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ፍርደኛ የሆነ ታራሚ መቀጮውን እስካልከፈለ ድረስ የአመክሮ ተጠቃሚ መሆን እንደማይችል ማስፈሩም በተግባር የአመክሮ ተጠቃሚው በሕግ የተመለከቱትን ሌሎች መስፈርቶች አሟልቶ እያለ በአመክሮ እንዳይለቀቅ እንቅፋት ይሆንበታል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት በወንጀል ሕጉና በመመሪያው መካከል የተፈጠሩ አለመጣጣሞች የአመክሮ አፈጻጸምን በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት አስቸጋሪ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ከነዚህ የሕግ ክፍተቶችና ከሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የመነጩ ችግሮች በአመክሮ አሰጣጡ ሥርዓት ላይ ሳንካን ሲፈጥሩ ተስተውለዋል፡፡ ሕጉ የያዛቸው አመክሮን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአፈጻጸም ወቅት ተገቢው ግንዛቤና ትኩረት ሳይሰጣቸው ተዘንግተዋል፡፡ አመክሮ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 መሠረት ታራሚዎች መልካም የሚባል የባሕርይ መሻሻል በማሳየታቸውና 2/3ኛውን የእሥራት ጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ ቀሪውን የፍርዱን 1/3ኛ ወይም በዚሁ ሕግ አንቀጽ 204 መሠረት በፍርድ ቤቱ የሚወሰነውን የሙከራ ጊዜ በአመክሮ ውስጥ በመሆን እንደሚፈጽሙ የተደነገገ ቢሆንም ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው አመክሮ የሚሰጠው የእሥራት ጊዜን ለመቀነስ ብቻ

እንደሆነ ነው፡፡ በአመክሮ የሚለቀቁ ታራሚዎች ቀሪውን የእሥራት ጊዜ በክትትልና በቁጥጥር ሥር ሆነው በፈተና እንደሚያልፉ ግንዛቤ ካለመኖሩም ባሻገር በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 205 (2) ሥር በአመክሮ የተለቀቁ ታራሚዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ አካል መኖር እንዳለበት ቢመለከትም በተግባር ሕጉ ሲፈጸም አይስተዋልም፡፡

ሌላው በወንጀል ሕጉ በአመክሮ ለመለቀቅ ቅድመሁኔታ ሆኖ ቢመለከትም በተግባር የማይፈጸመው ካሳ የመክፈል ግዴታ ነው፡፡ ታራሚው በወንጀል ድርጊቱ ጉዳት ያደረሰባቸው ተበዳዮችን ለጉዳቱ ካሳ መክፈል እንዳለበትና ይህም ለአመክሮ ቅድመሁኔታ እንደሆነና የዚህ ሁኔታ አለመሟላት አመክሮን ሙሉ በሙሉ ከሚያስከለክሉ ሁኔታዎች አንዱ መሆኑን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 (1) (ለ) እና በመመሪያው ቁጥር 6.1(3) ላይ ቢመላከትም በተግባር ግን ከግምት ውስጥ እንደማይገባና አመክሮን የማስከልከል ውጤት እንደሌለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመጨረሻም ከአመክሮ አፈጻጸም ጋር የሚነሳው ችግር ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ላይ የተመለከተው 2/3ኛ የእሥራት ቅጣት ጊዜ ስሌት ነው፡፡ ይህ የእሥራት ጊዜ ከፍርድ በፊት በፖሊስ ጣቢያ ወይም በመሰል ስፍራዎች ታራሚዎች ያሳለፏቸውን የእሥራት ጊዜያት ሊያካትት ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ታራሚው ከመቼ ጀምሮ በእሥራት ላይ እንደነበረ ሳይገለጽ 'እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ' የሚል የቅጣት ውሳኔ በሚተላለፍበት ጊዜና ትእዛዙ ብቻ ለማረሚያ ቤቶች እንዲደርስ ሲደረግ የአመክሮውን ጊዜ ለማስላት ችግር እንደሚያጋጥም በጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የመፍትሄ ሐሳቦች**

በጥናቱ መሰረታዊ የሆኑ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች አመክሮ በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እንዳይከናወን እንቅፋት እንደሆኑም በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ለችግሮቹ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ዋና ዋና ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አመክሮ በፍርድ ቤት አለመሰጠቱ ከኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ጋር በግልጽ ስለሚቃረን በፍርድ ቤት እንዲሰጥ ወይም ይህን የሚተካ አዲስ ሕግ ሥልጣን ባለው አካል መውጣት ይገባዋል፤
- እንደሌሎች ሀገሮች ሁሉ አመክሮን ከመነሻ እስከ መድረሻው በባለቤትነት ይዞ ሊሰራ የሚችል ገለልተኛ የሆነ ቦርድ ቢቋቋምና ሥራውን እንዲሰራው ቢደረግ፤
- መመሪያው ደጋጋሚነትን ያመላከተበት መንገድ ከወንጀል ሕጉ ጋር የተጣረሰ በመሆኑ የወንጀል ሕጉን መንፈስ በተከተለ መልኩ ቢሻሻል፤
- የወንጀል ሕጉ ደጋጋሚንና ልማደኛ ደጋጋሚን ለይቶ በማመላከት ልማደኛ ደጋጋሚን ለአመክሮ መከልከል እንደሁኔታ ቢያመላክትም የልማደኛ ደጋጋሚ ትርጉምና ሁኔታ በአግባቡ በሕግ ስላልተወሰነ ሕጉ ይህንን ግልጽ ሊያደርግ በሚችል መልኩ ቢሻሻል፤
- መመሪያው በከባድ ወንጀሎች ማለትም በሰው መግደል፣ በዘረፋ፣ በአስገድዶ መድፈርና በሌሎችም የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን የአመክሮ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መከልከሉ ከሀገሪቱ ሕገመንግሥትና የወንጀል ሕጉ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ቢሻሻል፤
- ታራሚዎች በአመክሮ ከተለቀቁ በኋላ ቀሪውን የእስር ጊዜ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሕግ አክባሪ ዜጋ ሆነው እየኖሩ መሆናቸውን የሚከታተል አካል

እንደሚቋቋም ሕጉ ቢደነግግም እስከአሁን እየተሰራበት ስላልሆነ በየወረዳው አስተዳደርና ጸጥታ ጽ/ቤት ባለሙያ ተመድቦ ሥራው እንዲሰራ ቢደረግ፤

- ስለ ታራሚው በቂ መረጃ ለማግኘት ሁሉም ፍርድ ቤቶች የእሥራት ቅጣት ሲወስኑ ታራሚው እጁ የተያዘበትንና ቅጣቱ መፈጸም የሚጀምርበትን ጊዜ በውሳኔው ውስጥ በግልጽ እንዲያሰፍሩ ቢደረግ፤ ታራሚው ወደማረሚያ ቤት ሲላክ የእሥራ-ት ትእዛዙና የፍርድ ግልባጩ ለማረሚያቤቱ እንዲደርሰው ቢደረግ፤
- በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በስምምነት ታራሚው ለተጎጅዎች የሚከፍለው የጉዳት ካሳ ካለ ይኸው መፈጸሙን ከአመክሮ በፊት ቢረጋገጥ።